በእግዚአብሔር ቃል ላይ በተጻፉት ማስረጃዎች መሠረት አስተማማኝ ዋስትና ያለው ነው። ያለፉትንና አሁን ያሉትን በታላቅ ማዳን ነፃ ባወጣውና በታረቀው ሰው ውስጥ ኃይል ባለው (ሮሜ.8፡29፤ 1 ዮሐ.3፡2፤ 2 ጴጥ.1፡4፤ 2ኛ ቆሮ.3፡18) እንዲህ ሰውን ወደ ቀድሞ ቦታውና ዓላማው ለሚመልሰው ለኢየሱስ ክብር ይገባዋል።

ሰው በዚህ አዲሱ ስፍራው እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ላለው ዓላማ ተካፋይ ይሆናል። ይህም ዓላማ ከዚህ የኃጢአትና የዕውርነት ዓለም ድነው ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ የሚፈልጉትን መርዳት ነው። እግዚአብሔር ሰውን የፍቅሩ መግለጫ እንዲሆን ስለፈጠረው አማኞች በዚህ ፍቅርና ዘላቂነት ባለው ከእግዚአብሔር ጋር የመቀራረብ ዕድል እየተደሰቱ እነርሱም በተራቸው ፍቅራቸውንና እምልኳቸውን በማያቋርጥ ሁኔታ ማቅረብ ይችላሉ። ይህን የእግዚአብሔርን ዓላማ የራስ አድርጎ መጠቀም ነው።

## 2. የወንጌሉ ማስረጃ

ከነዚህ አንዳንዶቹን አስቀድመን ተመልክተናቸዋል። ብዙ ሰዎች ሕይወታቸውን ለመገንባት የሚፈልጉት በሃይማኖታውያን ሰዎች ንግግር ላይ ሳይሆን እርግጠኛነትና ዋስትና ባለው መንገድ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ነው። ስለዚህ እውነቱ በተጨባጭ ማስረጃ እንዲቀርብላቸው ይፈልጋሉ። አንድ ሙስሊም መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ ሊታመንበት የሚገባ እርግጠኛ የእግዚአብሔር ቃል ነው ብሎ ለመቀበል በቂ ማስረጃዎች ይፈልጋል። ሐዋርያት ይህንን ዘዴ በብዛት ይጠቀሙበት ነበር (ሐዋ.2 ከቁ. 25 ጀምሮ፤ 3፡18-24፤ 1 ቆሮ. 15፡3፤ ሉቃ. 1፡1-4፤ ሐዋ. 1፡3፤ 1ኛ ዮሐ. 1፡1-3፤ 2 ጴጥ. 1፡16-21)።

ከላይ ከተጠቀሱት ጥቅሶች የሚከተለውን ማጠቃለያ መስጠት እንችላለን፡-

ሀ) ሐዋርያት የብሉይ ኪዳንን ትንቢቶች በመጥቀስ «ነገራቸውን» በትክክል በማስተላለፍ ሕዝቡ የትንቢቶቹን ፍጻሜ በመገንዘብ የሚያስተምሩትን እንዲቀበል ያደርጉ ነበር። ለምን እንደዚህ አደረጉ?

ለ) ጴጥሮስ ነገሩ ከተፈጸመ ከሰባት ሳምንታት በኋላ በኢየሩሳሌም ስለ ኢየሱስ ስቅለትና ሞት ሲናገር በዚያን ጊዜም ሆነ ከዚያ በኋላ ነገሩን ማወቅ የነበረባቸውና ሳይፈልጉት ለወንጌሉ የተጋለጡት አይሁዳውያን እነዚህን እውነቶች አልካዱም። እነዚህ የጴጥሮስ ዓረፍተ ነገሮች እውነትና በሁሉም ዘንድ የታወቁ ባይሆኑ ኖሮ አይሁዳውያን ምን ያደርጉ እንደነበር መገመት እንችላለን? (ሉቃ. 24፡18)።

ሐ) ጳውሎስ እጅግ ብዙ (እስካሁንም ያሉ) የዓይን ምስክሮችን ይጠቅሳል (1 ቆሮ. 15:3-6)። እኛ ምናልባት ይህን አባባል በቆሮንቶስ ያሉት ተጠራጣሪዎች ንግግሩን እንዲቀበሉ ለማበረታታት እንደተናገረ አድርገን እንወስደው ይሆናል። ከዚህ በተጨማሪ ጳውሎስ በተደጋጋሚ እነዚህ እውነቶች «መጽሐፍ እንደሚል» ማለትም በብሉይ ኪዳን ትንቢቶች መሠረት እንደተፈጸሙ ገልጿል።

መ) ሉቃስ ለጻፈው ነገር የዓይን ምስክሮች እንደነበሩትና «ሁሉን ከመጀመሪያው» ተከታትሎ «በየተራው» እንደጻፈ ይናገራል።

ሠ) ኢየሱስ ክርስቶስ ከስቅለቱና ከሞቱ በኋላ ለዓይን ምስክሮቹ «አርባ ቀን እየታያቸው በብዙ ማስረጃ ሕያው ሆኖ ራሱን አሳያቸው።» ለመሞቱ ምንም ማስረጃ አያስፈልግም። ሮማውያን ሥጋው እንዲወሰድ የፈቀዱት መሞቱ ከተረጋገጠ በኋላ ነው (ዮሐ. 19:33-37)።

ረ) ሐዋርያው ዮሐንስ መልእክቱን ሲጀምር ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ሕይወት የዐይን ምስክር እንደሆነ በእርግጠኝነት ይናገራል (1:7)።

ሰ) በተጨማሪም ጴጥሮስ በሰማዕትነት ከመሞቱ በፊት (2 ጴጥ 1:13-15) የክርስቶስን መለኮታዊነት የዓይን ምስክር ሆኖ ያረጋግጣል፤ ይህም ቢሆን ግን «ከእርሱ ይልቅ የጸናውን የትንቢት ቃል» ሳይጠቅስ አላለፈም።

የወንጌልን እውነት በማስረጃዎች በማስደገፍ ማቅረብ እንደሚያስፈልግ በመረዳታቸው ሐዋርያት እግዚአብሔር የሰጣቸውን ሁሉ በመጠቀም ነገራቸውን በታማኝነትና በጽናት ከማስረጃ ጋር አቅርበዋል። ታዲያ እኛ ስለምን እንዲህ አናደርግም? የእግዚአብሔር ነገር በእውነት ምን ያህል ጠንካራ እንደሆነ ሙስሊሞች ለማየት ይፈልጋሉ!

## 3. ወንጌሉ የሚጠይቃቸው ነገሮች ወይም ሁኔታዎች


ጌታ ሕዝቡን እንዲህ በማለት ጥያቄ ጠይቋቸው ነበር:-

> «ከእናንተ ግንብ ሊሠራ የሚወድ ... አስቀድሞ ተቀምጦ ኪሳራውን የማይቆጥር ማነው?» (ሉቃ 14:28)። ወንጌል መልካም ዜና ነው። ደግሞም መጥፎ ዜና ነው! መልካምን ዜና አንቀበልም ለሚሉት በእርግጥ ከፉ ዜና ነው። የተወሰነ ማሰብና ማሰላሰል ያስፈልጋል (ኢሳ. 1:18)።

ለምንመሰክርላቸው ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ሲመለሱ እግዚአብሔር ከነሱ የሚጠብቅባቸውን ነገሮች ቆም ብለው እንዲያስቡት ጊዜ ልንሰጣቸው ያስፈልጋል። ከነዚህም፡- ንስሐ (ለከአርጌው የሕይወት ኑሮ ወይም መንገድ መመለስ)፥ ጥምቀት (ሐዋ. 2፡38፤ 3፡19)፥ እምነት (ሐዋ 10፡43፡ 13፡38-39)፥ ለመታዘዝ መፍቀድ (ዕብ.5፡9) እና እስከ መጨረሻ መዝለቅ (ዕብ.3፡6፤ ራእይ 2፡10፤ ማቴ. 24፡13) የሚሉት ይገኙበታል። ኃጢአተኛው ደኅንነት ለማግኘት መጣር አለበት፤ እግዥ ደግሞ ያለ ቅድስና እግዚአብሔርን ማየት አይችልምና ቅድስናን መፈለግ አለበት (ዕብ. 12፡14፤ 1 ጴጥ. 1፡13-19)። በመጨረሻም እግዚአብሔር ከርሱ ጋር አብረን እንድንሠራ ይፈልጋል (ማቴ. 28፡18-20)። እንደገና እነዚህ ለብዙዎች እንግዳ የሆኑት ቃላት መተርጎም አለባቸው።

## 4. የወንጌሉ የተስፋ ቃሎች

በዚህ አስደናቂ በሆነ ማስታወሻ አቅርቦታችንን ማጠቃለል እንችላለን። እንዴት ያለ የተትረፈረፈ ተስፋ፥ ደስታና መፅናናት ነው ጌታ ለእኛ የሰጠን! እስቲ እናስተውለው፡- ምሕረቱን (መዝ. 103፡7)፥ ይቅርታውን (መዝ. 103፡12፤ ኢሳ. 59፡2፤ 43፡25፤ 44፡22፤ ኤር. 31፡34)፥ የዘላለም ሕይወት (ዮሐ. 10፡22-28፤ ማቴ. 25፡34፥ 46 ለ)፥ በዚህ በምድር ላይ አዲስ ዓይነት ሕይወት (2 ቆሮ 5፡17)፥ ዕረፍት (ማቴ 11፡28፥ ራእ. 14፡13)፥ ዘለቄታ ባለው ሁኔታ ከእኛ ጋር መሆኑን (ማቴ 28፡20) ሁሉ አረጋግጦልናል። ዓለም በሙሉ ሊያገኘው የሚፈልገውን፥ ነገር ግን የትም የማያገኘውን ነገር ፍቅርን፥ ደስታንና ሰላምን ሊሰጠን ይፈልጋል (ዮሐ. 14፡27፤ 15፡9፥11፤ ገላ. 5፡22)። በተጨማሪም የሚወዳቸው የሚነግሡባትን (ራእ. 5፡10) መንግሥተ ሰማይን እንደሚሠጠን ቃል ገብቶልናል (ዮሐ.



14፡3)። እንዲሁም በምድር ላይ ያለውን ሥራችንን በሚገባ እንድንፈጽም የሚያስፈልጉን ስጦታዎች ተሰጥተውናል (1 ቆሮ. 12፡8-10፤ ኤፌ. 4፡11፤ ሮሜ. 12፡6-8፤ ሐዋ. 2፡38 ለ)።

በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ በታማኝነትና ልብን በሚመረምር ሁኔታ ራሳችንን ጥያቄ መጠየቅ አለብን። የሰው አዕምሮ፥ ልብና ኅሊና ባሁኑና በሚመጣው ዓለም ሙሉ በሙሉ ከመርካትና ከመጥገብ ሌላ የሚፈልገው ነገር አለን? ወንጌላችን በይዘቱ፥ በማረጋገጫና በማስረጃ፥ በማንኛውም አቅጣጫ ከሚያቀርበው በተቀራረበ ሁኔታ ሊያቀርብ የሚችል ሌላ ሃይማኖት ወይም እምነት አለን?

አንባቢው እነዚህን ጥያቄዎች በዕውቀትና በታማኝነት መመለስ ከቻለ፥ በጭራሽ ምንም የለም የሚለውን መልስ መስጠት መቻል አለበት። ስለዚህ እስካሁን ለሰው ልጅ የተሻለ ነገር በማቅረብ፥ በተጨማሪም እውነቱን በማስረጃዎች አስደግፎ ማንም ሊያቀርብ እንዳልቻለ እርግጠኞች መሆን እንችላለን እስኪ እንግዲህ በልበ ሙሉነት፥ በፍቅርና በዕውቀት ይህንኑ የወንጌል መልእክት እናካፍል! (ዕብ. 13፡12-13)።

ቢሆንም እንኳ በሙስሊሞች መሐል ምላሹ አስገራሚ ላይሆን ይችላል። ፍራንሲስ ሼፈር ይህንን በራሱ መንገድ በትክክል ገልጾታል።

> «እውነተኛ የሆነው መነቀፍ የሚመጣው አንድ ሰው በታማኝነት ሲሰብክ ነው፤ በዚህ ጊዜ ዓለም በዐመፅዋ ምክንያት ከእውነቱ ፈቀቅ ትላለች። ሰዎች አንቀበልም የሚሉትም የሚነገራቸው ነገር ትርጉም ስለማይሰጣቸው ሳይሆን፥ ለእግዚአብሔር መስገድ ስለማይፈልጉ ነው። ይህ ‹የመስቀሉ ስደት› ነው»።

መስቀሉ የሚያመለክተው ሰው ራሱን ማዳን አለመቻሉን ነው። ይህ ደግሞ ክቡር ነኝ በሚለው ትዕቢተኛ ሰው ላይ የሚወርድ ከፍተኛ የሆነ ውርደት ነው። ለአሁንና ለዘላለም ያለው ብቸኛ ተስፋው ይኸው ነው።

የወንጌሉ ይዘት ይኸ ሁሉ እና ከዚህም የላቀ ነው። ይህንን ወደ ተራ ነገር ወይም ወደ መደበኛ ንግግር ዝቅ ማድረግ ለወንጌል የማይበጅና ብቃት የሌለው ከመሆኑም በላይ ዋናውን ነገር ሙሉ በሙሉ መሳት ነው። ወንጌልን መስበክ ማለት የእግዚአብሔርን የፍቅር ታሪክ፥ በእኛ ሙሉ በሙሉ ተስፋ መቁረጡን፥ ለእኛ መሠቃየቱንና ከእኛ የሚጠብቃቸውን እንዲሁም ያከናወናቸውን ነገሮች መናገር ማለት ነው፤ (ኤፌ. 1፡23፤ 4፡13)።

የዚህ ወንጌል ክፍል እያንዳንዱ ሊገባ በሚችል መልኩ መቅረብ አለበት። እንዲሁም አድማጩ (ልባችን በዚህ ነገር ላይ እንዳለ ማወቅ አለበት። ይህ ደግሞ ‹የተቀነባበረ የሥነ-መለኮት ትምህርት› ሳይሆን የፍቅሩን/ የፍቅርዋን ሕይወት መግለጽ ማለት ነው። (ይህ ሐሳባዊው ክፍሉ ሲሆን)፣ ተጨባጩ ደግሞ ዘወትር በመጽሐፍ ቅዱስ የተደገፈ መሆን አለበት።

## መንፈሳዊ ጦርነት

ምናልባት ለሙስሊሞች ወንጌልን ስለ ማድረስ ዕውቀት፣ መረዳትና ዘዴዎች ሁሉ ሲባል፣ ስለ ጸሎት ምንም ሳይነካ ሲቀር ትደነቅ ይሆናል። ይህ ማለት ጸሎት ዝቅተኛ ሚና መጫወት አለበት ማለት ነው?

በፍጹም አይደለም! ባንፃሩ ከፍተኛ ሚና ስላለው ነው ይህ ረጅም ምዕራፍ የተመደበለት።

እስቲ በመጀመሪያ ነገሩን በጥቅሉ ላስቀምጠው።

ለሙስሊሞች ወንጌልን በማድረስ ውስጥ ሦስት ነገሮች አሉ፦

መረዳትና ዕውቀት

ጸሎት

ተግባራዊ ልምምድ

አንዱ ለሌላው ምትክ ሊሆን በፍጹም አይችልም!

በእርግጥ ይህ ከመጀመሪያ ጀምሮ የሚያስፈልግ ቢሆንም ተግባራዊ ልምምድ በዚህ ነገር ላይ መጨመር አለበት። እስቲ አሁን ስለ ጸሎትና መንፈሣዊ ጦርነት ፅንሰ ሐሳብ እንመልከት።

በመጀመሪያ ደረጃ ይህ የሚያመለክተን በእግዚአብሔርና በሰይጣን፣ በእግዚአብሔር መንግሥትና በጨለማው ግዛት መካከል፣ በውስጡ ያሉትን አባላት በሙሉ የሚያካትት ጦርነት እንዳለ ነው። ይህ አባባል በመሠረቱ አዲስ ስለሆነ ማብራሪያ ያስፈልገዋል።

ምናልባት አብዛኞቻችን ጦርነት በመሠረቱ ምን እንደሚመስል እናውቅም ወይም ጥቂት ዕውቀት ይኖረን ይሆናል። ጦርነት እጅግ በጣም አስከፊ፣ አውዳሚ፣ አጥፊና በተቀናቃኙ ላይ ሙሉ በሙሉ ድልን ለመቀዳጀት ታልምና ታስቦበት የሚደረግ

የመጨረሻ ደረጃ የትግል ዓይነት ነው። አንዳንድ ጊዜ ይህ ግልጽ ጦርነት በረድ ይልና ‹ቀዝቃዛ ጦርነት› ይሆናል። ነገር ግን ይህ የጦርነቱን ሥልት እንጂ መሠረታዊ እውነቱንስ አይቀይረውም።

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ‹በሰማያዊ ስፍራ ጦርነት› እንዳለ ወይም ስለ ‹ጦር መሣሪያዎቻችን› እናነባለን። በዚህም ዓለም በትክክልና በስሕተት፥ በዕውነትና በማታለል መካከል ያለውን ከፍተኛ ትግል ለማየት እንችላለን። ውሸት፥ ክፋትና ማታለል ባለማቋረጥ እየጨመረ ነው። የታይታ መንፈሳዊነትና የኃዘኔታ ፍቅር እያሳቀበ ሄዷል። የአድር ባይነትን አቅጣጫ አለመያዝ ዛሬ በብዙ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ‹ጥበብ የጎደለው› እና ‹ኋላ ቀር ወግ አጥባቂነት› ተደርጎ ተወስዷል። ሌሎች ደግሞ በግልጽ ከጠላት ጋር ተወዳጅተው የጋራ ዓላማና ፍላጎት ይዘው ይራመዳሉ።

የምንፈልገውን ግልጽ በማድረግ ጉዳያችንን የበለጠ ልናሰምርበት ያስፈልጋል። «ከእግዚአብሔር እንደሆንን ዓለምም በሞላው በክፉው እንደተያዘ እናውቃለን» (1 ዮሐ 5፡19)። ይህ ደግሞ ከመጠን በላይ ብዙዎችንም የሚያናድዳቸው ዐረፍተ ነገር ነው። ነገር ግን እውነት ነው።

## ትንተና

እስቲ በጥቅሉ ይህን ፅንሰ ሐሳብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነ ግምገማ ተመልክተን «መንፈሳዊ ጦርነት» የሚሉ ቃላት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደሌለ እንናገር። ታዲያ በመጽሐፍ ቅዱስ እኛን ለማነቃቃትና ለማበረታታት ‹እንደ ክርስቶስ በጎ ወታደር› (2 ጢሞ. 2፡3) ‹መልካሙን ገድል ተጋደል› (1 ጢሞ. 1፡18፤ 6፡12፤ 2 ጢሞ. 4፡7)፥ እያለ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው ምንድነው? (ቃሉ መጀመሪያ በተፃፈበት በግሪክ ገድል ወይም መጋደል ከፍተኛ የሆነ መከራን የሚያመለክት መሆኑን መገንዘብ ጠቃሚ ነው)። ምናልባት ተስፋ በሚያስቆርጥ ሁኔታ ይህን ርዕስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጥቂቱ ይሆናል የምናገኘው፡-

> «. . . በአንድ ልብ ስለ ወንጌል ሃይማኖት አብራችሁ እየተጋደላችሁ በአንድ መንፈስ እንድትቆሙ ስለ ኑሮአችሁ እሰማ ዘንድ . . .» (ፊል. 1፡27)።
>
> «ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና . . . በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት» (1 ጴጥ. 5፡9)።
>
> «. . . እንድታግዛቸው እለምንሃለሁ. . . በወንጌል ከእኔ ጋር አብረው ተጋድለዋልና» (ፊሊ. 4፡3)።

«. . . ወደ እግዚአብሔር እየጸለያችሁ ከእኔ ጋር ትጋደሉ ዘንድ. . . እለምናችኋለሁ» (ሮሜ. 15፡30)።

«እኛም በክርስቶስ ፍጹም የሚሆን ሰውን ሁሉ እናቀርብ ዘንድ ሰውን ሁሉ እየገለጽን፥ ሰውንም ሁሉ በጥበብ ሁሉ እያስተማርን፥ የምንሰብከው እርሱ ነው። ስለዚህም ነገር ደግሞ በእኔ በኃይል እንደሚሠራ እንደ አሠራሩ እየተጋደልሁ እደክማለሁ። ስለ እናንተና በሎዶቅያ ስላሉት ፊቴንም በሥጋ ስላላዩት ሁሉ እንዴት ያለ ትልቅ መጋደል እንዳለኝ ልታውቁ እወዳለሁና. . .» (ቆላ. 1፡28-2፡1)።

«መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለም . . . ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዥዎች ጋር በሰማያዊም ሥፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳዊያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ» (ኤፌ. 6፡12)።

«ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋል፤ ዓለምንም የሚያሸንፈው እምነታችን ነው» (1 ዮሐ. 5፡4)።

«እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ከምስክራቸውም ቃል የተነሣ ድል ነሡት . . .» (ራእ. 12፡22)።

እንድንታገል፥ ፀንተን እንድንቆም፥ እንድንጋደል፥ እንድንቃወምና ድል እንድናደርግ ጥሩ መመሪያዎች ተሰጥተውናል፡-

«በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ። የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ። መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካሉት ከክፋት መንፈሳዊያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ። ስለዚህ በክፉው ቀን ለመቃወም፥ ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሡ እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ፥ የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ፤ በሁሉም ላይ ጨምራችሁ የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነትን ጋሻ አንሡ፥ የመዳንንም ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ፤ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው። በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ፤ በዚህም አሳብ ስለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ ትጉ ደግሞ የወንጌልን ምሥጢር በግልጥ እንዳስታውቅ አፌን በመክፈት ቃል ይሰጠኝ ዘንድ ስለ እኔ ለምኑ» (ኤፌ. 6፡10-19)።

በከፍተኛ ደረጃ እንደ ክርስቲያን እንድንገነዘበው የተደረገው አውቀነውም አላወቅነውም፥ ወደድነውም ጠላነውም በ ‹በሰማያዊ ሥፍራ ካሉ በክፉት መንፈሳውያን ኃይላት› ጋር ‹መጋደል› እንዳለብን ነው።

ወንጌልን ማሠራጨት በተለይም በሌላ ሃይማኖትና ባህል ባሉት መሐል ሁልጊዜ መንፈሳዊ ጦርነት ነው። ወንጌልን በማሠራጨት በሰይጣን ባርነት የታሰሩትን ነጻ ለማውጣት ነው የምንፈልገው። ስለዚህ ይህ አጸፋዊ የሆነ ጥቃት አለበት። ስለዚህም ጉዳይ በመጽሐፍ ቅዱስ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶናል።

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ራሱ ልምድ አንዳንድ ሐሳብ ይሰጠናል፡-

> «እኔም በድካምና በፍርሃት በብዙ መንቀጥቀጥም በእናንተ ዘንድ ነበርሁ፤ እምነታችሁም በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ እንዳይሆን ቃሌም (ይዘቱ) ስብከቴም (ቅርጹ) መንፈስንና ኃይልን በመግለጥ ነበረ እንጂ በሚያባብል በጥበብ ቃል አልነበረም» (1 ቆሮ 2፡3-5)።

በተጨማሪም ይህን እናነባለን፡-

> «ወንጌላችን በኃይልና በመንፈስ ቅዱስ በብዙ መረዳትም እንጂ በቃል ብቻ ወደ እናንተ አልመጣምና . . .» (1 ተሰ. 1፡5)።

## ኃይል በወንጌል ስርጭት ውስጥ

ማናችን ነን የእግዚአብሔርን ኃይል፥ የመንፈሱን ኃይል ለመግለጽ እንድንችል ፍላጎት ወይም ስሜት የሌለን? በተለይም በዚህ ክፍለ ዘመን ብዙ ሐሳብ፥ ክርክርና ጸሎት በዚህ ጥያቄ ላይ አለ። ብዙ መጻሕፍት ተጽፈዋል እንዲሁም ብዙ ‹ኃይለኛ ሰባኪዎች› መጥቷል፤ ሄደዋል። በተጨማሪም በዚህ ርዕስ ምክንያት በቤተ ክርስቲያን ብዙ መከፋፈል ሲከሰት ኖሯል።

እስቲ በዚህ ዋና ነጥብ ላይ መጽሐፍ ቅዱሳዊና መንፈሳዊ መልስ ለመስጠት እንሞክር።

1. ኃይሉን የያዝነው እኛ ሳንሆን እግዚአብሔር ነው።

«ነገር ግን የኃይሉ ታላቅነት ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ እንዳይሆን ይህ መዝገብ (ስለ እግዚአብሔር ክብር ከእግዚአብሔር የዕውቀት ብርሃን) በሸክላ ዕቃ ውስጥ (ማለትም እኛ ምድራዊ ስብዕና ያለን ነን) አለን» (2 ቆሮ. 4፡7)።

2. በእኛ ድካም ውስጥ እግዚአብሔር ኃይሉን ይገልጻል።

«በመገለጥ ታላቅነት» ምክንያት እንዳይታበይ ለማድረግ ጳውሎስ «የሥጋ መውጊያ» ተሰጠው፤ ይህ ነገር ምንም ይሁን በደስታ ተቀብሎታል።

«እንግዲህ የክርስቶስ ኃይል ያድርብኝ ዘንድ በብዙ ደስታ በድካሜ ልመካ እወዳለሁ» (2 ቆሮ. 12፡9)።

3. የእግዚአብሔር ኃይል የሚገለጸውና የሚሠራው በወንጌሉና በክርስቶስ መስቀል አማካይነት ነው!

«በወንጌል አላፍርም ... ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና» (ሮሜ. 1፡16)።

«የመስቀሉ ቃል ... የእግዚአብሔር ኃይል ነውና!» (1ኛ ቆሮ. 1፡15)።

ለዚህ ጠበቅ ያለው ትርጉም የሚገኘው መስቀሉ ለሰዎች ‹የማሰናከያ ድንጋይ› ወይም በዐይናቸው ፊት ‹ሞኝነት› መሆኑ ነው፤ በተጨማሪም ዕንቅፋት ነው፤ (1 ቆሮ. 1፡23 እና 18፤ ገላ. 5፡11)። በዚያው መልኩ ክርስቶስ የዕንቅፋት ድንጋይ ነው (1 ጴጥ. 2፡8)። ምንድነው እንዲህ የሚያሰናክል? ሞኝነት የሆነው? እንዲሁም ዕንቅፋት የሆነው› ዓውደ ንባቡ (አገባቡ) ይህን በግልጽ ያመለክታል፡-

**ይህ ነገር የሰው ራሱን በ ‹መልካም ሥራዎች› ወይም በሌላ በምንም መንገድ ማዳን እንደማይችል ይገልጻል፤ በተጨማሪም ሙሉ በሙሉ እግዚአብሔር ሠርቶ በጨረሰው ነገር ላይ ጥገኛ መሆኑን ያሳያል! ሰው ራሱን ችሎ የመቆም ፍላጎት አለው! እንደ ለማኝ ጥገኛ መሆን አይፈልግም።**

የመስቀሉ መልእክት የሆነው ወንጌል ብቻ ደኅንነትን፥ መንፈሳዊ አኗኗርንና የማገልገል ችሎታን የሚያስገኝ የእግዚአብሔር ኃይል አለው!

«በበጎ ሥራ ሁሉ ፍሬ እያፈራችሁ በእግዚአብሔር ዕውቀት እያደጋችሁ ከደስታም ጋር በሁሉ በመጽናትና ለመታገስ እንደ ክብሩ ጉልበት መጠን በኃይል ሁሉ እየበረታችሁ ... ለጌታ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እንለምናለን» (ቆላ 1፡10-12)።

«የመለኮቱ ኃይል በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን በማወቅ ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚሆነውን ነገር ሁሉ ስለሰጠን ...» (2 ጴጥ 1፡3)።

ይህንን ሲል «የመንፈሱ ኃይል መገለጽ» ማለቱ እንደሆነ እናምናለን።

## እንዴት ነው «የምንዋጋው»?

«በሰው ልማድ ምንም እንኳ የምንመላለስ ብንሆን እንደ ሰው ልማድ አንዋጋም፤ የጦር ዕቃዎችን ሥጋዊ አይደለምና ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት

> ብርቱ ነው፤ የሰውንም አሳብ በእግዚአብሔርም ዕውቀት ላይ የሚነሣውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን፤ ለክርስቶስም ለመታዘዝ አዕምሮን ሁሉ እንማርካለን» (2 ቆሮ. 10፡3-5)።

በዚህ ቦታ ‹ውጊያ› የሚለው ቃል (በግሪኩ ስትራቱዎ) ትኩረት የተሰጠው ነገር ነው። ‹የጦር ዕቃችን› የሚለው ‹የውጊያችን መሣሪያዎች› (በግሪኩ ስትራቲያ) ተብሎ ቢነበብ መልካም ነው። የግሪኩ ‹ስትራቶስ› የሚለው ቃል በካምፑ የሠፈር ሠራዊት ማለት ነው፤ ይህም ወታደራዊ ግጭት እንዳለ ያመለክታል። በዚህ ላይ በግልጽ እንደሚታወቀው ግጭቱ መንፈሳዊ ነው።

ሰዎችን የሚያስረውና እግዚአብሔር ለጠፋው ሰው የሰጠውን ብቸኛ፥ ዋጋ ያለውና እውነተኛ ነገር እንዳያዩ የሚያሳውረውን የሰይጣን ኃይል ስለ መዋጋት በምናገርበት ጊዜ ከላይ የተጠቀሰው ቁልፍ የሆነ ጥቅስ ነው። እኔ እንደገባኝ ከዚህ ቀጥሎ ያለውም ከላይኛው ጋር የተያያዘ ሐሳብ አለው:-

> «መንፈስ ግን በግልጥ:- በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያዳመጡ ሃይማኖትን ይክዳሉ ይላል» (1 ጢሞ. 4፡1)።

እዚህ ላይ አገባቡን አውጥተን ብናየው የተጻፈውን የሚያዛባ ነገር አይመስለኝም። እስቲ ከላይ ያሉትን ጥቅሶች የሚሉትን በአንድነት ለማስቀመጥ እንሞክር:-

1. በእግዚአብሔር ዕውቀት ላይ የሚነሡና ራሳቸውን ከፍ አድርገው የሚያስቀምጡ ክርክሮችና አባባሎች አሉ።
2. ሰዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውን የክርስትና እምነት ትተው አታላይ መናፍስትንና ሀሊና በሌላቸው ግብዝ ውሸታሞች አማካይነት የአጋንንትን ትምህርት ይከተላሉ።
3. እነዚህን ክርክሮችና አባባሎች በእርግጥ መለኮታዊ ኃይል ባለው በ ‹ጦር ዕቃችን› እንሰብራቸዋለን፤ (መስበርም አለብን)።
4. ይህ የሚያስከትለው ‹በአለቆች፥ በሥልጣናት፥ በዚህ የጨለማ ዓለም ገዢዎችና በሰማያዊ ስፍራ ባሉ የክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት» ላይ ጦርነት ማወጅን ነው (ኤፌ. 6፡12)።
5. ይህ ዓይነቱ ጦርነት ዓለማዊ ጦርነት አይደለም፤ ነገር ግን በተቃራኒው መንፈሳዊ ጦርነት እንለዋለን።

እስቲ በመጀመሪያ ሁለት ጥያቄዎችን ለመመለስ እንሞክር:-

ሀ. ዓለም ጦርነት የሚያውጀው እንዴት ነው? (በተጨማሪ በግለሰቦች ወይም በፖለቲካ ቡድኖች መካከል እንዴት ነው)? በኃይል፥ በማታለል፥ በማድባት፥ በድርድር፥ በማውገዝ፥ በውሸት፥ በግድያ በሐሰት ፕሮፓጋንዳ፥ በማስፈራራት ወዘተ ...።

ለ. እኛ የምንዋጋባቸው መሣሪያዎች› ምንድናቸው? አሁን እነዚህን እናነባለን:- እውነት፥ ጽድቅ፥ ወንጌል መስበክ፥ እምነት፥ ደኅንነት፥ የእግዚአብሔርን ቃል አጥብቆ መከተል ናቸው። በተጨማሪም ሌሎች ክፍሎችን:- 2 ቆሮ.4:2፤ ቆላ. 4:8 ወዘተ ብናነብ መልካም ነው።

በተጨማሪም ውሸተኞች እነማን ወይም ምን እንደሆኑ መመልከት አለብን። ጌታችን ዲያብሎስን በውሸታምና የውሸት አባት ብሎ እንደሚጠራው እናውቃለን (ዮሐ 8:44)። ‹መንፈሳዊ ውሸቶች› መንፈሳዊውን እውነት እንዲቃረኑ፥ እውነት በታ እንዳይኖረው ለማድረግ ወይም ቢያንስ ቢያንስ ፈላጊውን ግራ ለማጋባት ተደርገው የተፈጠሩ እንደሆኑ ግልጽ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ሐሰተኞች እነማን እንደሆኑ በግልጽ አስቀምጧል፤ ማለትም:- የውሸት አባት ተባባሪዎች የሆኑ ሰዎች:-

> «እውነትን የምታውቁ ስለሆናችሁ:- ውሸትም ሁሉ ከእውነት እንዳልሆነ ስለምታውቁ እንጂ እውነትን ስለማታውቁ አልጽፍላችሁም። ክርስቶስ አይደለም ብሎ ኢየሱስን ከሚክድ በቀር ውሸተኛ ማን ነው? አብንና ወልድን የሚክድ ይህ የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው። ወልድን የሚክድ ሁሉ አብ እንኳ የለውም በወልድ የሚታመን አብ ደግሞ አለው» (1 ዮሐ. 2:21-23)።
>
> «የሰውን ምስክር ብንቀበል የእግዚአብሔር ምስክር ከእርሱ ይልቅ ይበልጣል። ስለ ልጁ የመሰከረው የእግዚአብሔር ምስክር ይህ ነውና። በእግዚአብሔር ልጅ የሚያምን በነፍሱ ምስክር አለው። በእግዚአብሔር የማያምን እግዚአብሔር ስለ ልጁ የመሰከረውን ምስክር ስላላመነ ሐሰተኛ አድርጎታል። እግዚአብሔርም የዘላለምን ሕይወት እንዲሰጠን ይህም ሕይወት በልጁ እንዳለ ምስክሩ ይህ ነው» (1 ዮሐ. 5:9-11)።

እዚህ ላይ ትንሽ ቆም ማለት አለብን። ይህ በእርግጥ ‹ጠንካራ ንግግር› ነው። አንድ ሰው፥ ግድ የለም ብሎ እንደዚህ ዓይነት ንግግሮችን መናገር ይችላል? መጽሐፍ ቅዱስ ግን ይህን ያደርጋል! በእርግጥ ይህ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን መጽሐፍ ስናነብ እንደምናስበው መሐመድ ከመምጣቱ በፊት ነው። እንደዚህ ያሉትን ሐሳቦች ማሰብ ነውን? እዚህ ላይ መጠቆም የምፈልገው ነገር ቢኖር፥ ነገሩ ያለው በቆምንበት

መንደርደሪያ ሐሳብ ላይ ነው። የምንፈልገው ‹ዓለም እንደሚያደርገው ጦርነትን ለማወጅ› ነው ወይስ የክርስቶስ አስተሳሰብ እንዲኖረን ነው? እውነትን ማፈን የእግዚአብሔር ቁጣ እንዲገለጥ መጠየቅ ነው፤ (ሮሜ. 1፡18)።

## ምሳሌአችን

ፍጹም የሆነውን ምሳሌ መመልከት ስንፈልግ፥ ኢየሱስ ክርስቶስን እንመለከታለን። ለጠፉት ኃጢአተኞች እንዴት ይናገር እንደነበር ስናስተውል የምንማረው:-

1. እውነትን ከመግለጥ በፍጹም ወደኋላ አላለም።
2. ተራ ንግግር እየተናገረ ሰዎችን ግራ አላጋባም። ነገር ግን እያንዳንዱን ሰው በግል፥ በራሱ ወይም በራሷ የመረዳት ችሎታ ልክ እንዳደረሰ በኃጢአታቸው ወይም ታማኝነት በማጉደላቸው ምክንያት የተያዙበትን ትክክለኛ ችግር እየገለጸ ረድቷቸዋል።
3. ይህንንም ያደረገው እየፈረደባቸው ሳይሆን በርኅራኄ ነው። ምክንያቱም እስከ መጨረሻው ደረስ ስለወደዳቸው የኃጢአተኞችን ኃዘን ይካፈላል (ዮሐ. 13፡1)። ‹በሁሉም መንገድ ወንድሞቹን ስለመሰለ› (ዕብ. 2፡17) ‹መሐሪና ታማኝ ሊቀ ካህን› ሆነ። ‹ከኃጢአት በስተቀር እንደ እኛው በሁሉ ስለተፈተነ› ‹በድካማችን ሊራራልን ይችላል› (ዕብ. 4፡15)።

በተመሳሳይ መልኩ ጴጥሮስ በበዓለ ሐምሳ ቀን በሺህ ለሚቆጠሩት አይሁድ በግልጽና በድፍረት ተናግሯል። በውጤቱ ሕዝቡም ‹ልባቸው ተነካ›። ለእነርሱ ጠቃሚ ነገር ነበር። ይህንኑ በእስጢፋኖስም ሲፈጸም እናያለን። መንፈስ ቅዱስን ተሞልቶ ነበር የተናገረው። አድማጮቹ ቁጣቸው ነድዶ ‹ጥርሳቸውን አፋጩ›። ‹ጆሮአቸውንም ደፍነው በሙሉ ኃይላቸው ጮሁ›። መልእክቱንም ተቃወሙት!

በእርግጥ እንደማንኛውም ሃይማኖት ሁሉ እስልምናም እውነትና ብርሃን አምጪ ሆኖ ቆሟል። «አያስደንቅም» ይላል መጽሐፍ ቅዱስ። «ይህ ድንቅ አይደለም፤ ሰይጣን ራሱ የብርሃን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና። እንግዲህ አገልጋዮች ደግሞ የጽድቅን አገልጋዮች እንዲመስሉ ራሳቸውን ቢለውጡ ታላቅ ነገር አይደለም» (2 ቆሮ. 11፡14)። ይህ ነገር «ጠላት» አረምን (በግሪክ ዚዛአንዩን ለ እንክርዳድን) በስንዴው መሐል እንደሚዘራ ከሚናገረው የክርስቶስ ትምህርት ጋር ይዛመዳል፤ (ማቴ 13፡ ከ24 ጀምሮ)። የሚያሳዝነው ነገር ማሳው የማያምር ሆኖ መታየቱ ሳይሆን የተዘራው አረም በጣም መርዛማና ከስንዴው ለመለየት እጅግ አስቸጋሪ መሆኑን ነው!

እንግዲህ መንፈሳዊ ጦርነት የጥቃት ዒላማው አድርጎ የሚያተኩረው በተታለሉት ላይ ሳይሆን፥ በአታላዩ ላይ ነው፤ ማለት በሰይጣንና በመላእክቱ።

## አታላይና የክልል መናፍስት

መንፈሳዊ ውጊያችን በየት አቅጣጫ መሆን እንዳለበት ለመለየት በምናደርገው ጥረት በዳንኤል ላይ ያለውን እንግዳ የሆነውን ክፍል ልንተወው አይገባም። ዳንኤል በሐዘን (!) ልብ3 ሣምንታት በፆም ቆየ። ከዚህም በኋላ በጤግሮስ ወንዝ ዳር ራእይ መጣ። ዳንኤል ሌሎች ሊያዩት የማይችሉትን ነገር አየ። ‹በፍታ የለበሰውን ጥሩም ወርቅ በወገቡ ላይ የታጠቀውን ሰው አየ። አካሉም እንደ ብርሌ ይመስል ነበር፤ ፊቱም እንደ መብረቅ ነበር፤ ዓይኖቹም እንደሚበለበል ፋና፥ ክንዶቹና እግሮቹም እንደጋለ ናስ፥ የቃሉም ድምፅ እንደ ብዙ ሕዝብ ድምፅ ነበር›። እጅግ የፈራውን ዳንኤልን አረጋግቶ እንዲህ ብሎ ተናገረው፡-

> «ዳንኤል ሆይ፥ አትፍራ ልብህ ያስተውል ዘንድ ሰውነትህም በአምላክህ ፊት ይዋረድ ዘንድ ካደረግህበት ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ቃልህ ተሰምቶአል፤ እኔም ስለቃልህ መጥቻለሁ። የፋርስ መንግሥት አለቃ ግን ሀያ አንድ ቀን ተቋቋመኝ። እነሆም፥ ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ። እኔም ከፋርስ ነገሥታት ጋር በዚያ ተውሁት። እርሱም እንዲህ አለኝ፡- ‹ወደ አንተ የመጣሁት ስለ ምን እንደሆነ ታውቃለህን? አሁንም ከፋርስ አለቃ ጋር እዋጋ ዘንድ እመለሳለሁ። እኔም ስወጣ፥ እነሆ የግሪክ አለቃ ይመጣል። ነገር ግን በእውነት ጽሑፍ የተፃፈውን እነግርሃለሁ። በዚህም ነገር ከአለቆቻችሁ ከሚካኤል በቀር ማንም የሚያጽናናኝ የለም» (ዳን. 10፡12-13፥ 20-21)።

እንደገና ግልጽ የሆነ አስተምህሮአዊ መልሶች ለመስጠት ውሱንነታችን ይሰማናል። በመጽሐፍ ቅዱስ በተለይም ከዚህ ከማይታየው ዓለም ጋር የተያያዙት ነገሮችን በሰብአዊ አዕምሮአችንና መንፈሳችን ሙሉ በሙሉ ልንረዳቸው የማንችላቸውና በጥቂቱ ብቻ የምንገነዘባቸው ብዙ ነገሮች አሉ። ቢሆንም ቅሉ ነገሩ በእርግጥ ያለ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም።

በዚህ ክፍል ላይ የምንማረው ቢኖር ሰማያዊ አካላትም ሳይቀሩ በአጋንንት ወይም በሰይጣን ኃይላት ሊታገዱ እንደሚችሉ ነው። እዚህ ላይ «በፍታ የለበሰው» ኢየሱስ ክርስቶስ ሳይሆን አይቀርም የሚለውን ሐሳብ ወደ መቀበሉ እናዘነብላለን። ከሌሎች

የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መረዳት እንደምንችለው:- በእዚህ ላይ በእርግጥ ድብቅ መንፈሳዊ ትርጉም እየሰጠን አይደለም:- ሰይጣን በወደቁት መላእክትና የአጋንንት ሠራዊት ኃይላት ላይ ገዢ ነው። እነዚህ ደግሞ አጋንንታዊ በሆነ የሥልጣን ተዋረድ በደንብ የተዋቀሩ ናቸው። የ «ፋርስ አለቃ» እና የ «ግሪክ አለቃ» ምናልባት የየራሳቸውን ክልል ለመቆጣጠር የታዘዙ ዋንኛ አጋንንቶች ይሆናሉ። ከዚህ እንደምንረዳው ሁሉም አገሮች፥ ወይም ጎሣዎች፥ ወይም የሃይማኖት ቡድኖች ዘወትር የሚጠብቋቸው፥ የሚመሯቸውና የሚቆጣጠሯቸው የአጋንንት አለቆች እና ትምህርቶች አሉባቸው ማለት ነው። ከዚህ የተነሣ ግለሰቦችና ብዙ ሰዎች ይታለላሉ፤ ይስታሉ፤ እንዲሁም ይታወራሉ። ምናልባትም እያንዳንዱ ጎሣ፥ የከተማ ወይም የመንደሩ ኅብረተሰብ፥ እያንዳንዱ መስጊድ፥ የአሕዛብ የማምለኪያ ቦታዎችና እንደቃሉ የማይመላለሱ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በተወሰኑ አጋንንቶች ቁጥጥር ስር ናቸው ለማለት እንችላለን።

ከዚህ የምንማረው ምንድነው? እንዲሁም ማድረግ ያለብንና የምንችለው ነገር ምንድነው?

1. «በፍታ የለበሰው ሰው» በሚካኤል ተረድቷል።
2. ዳንኤል እንዲረዳው አልተጠየቀም። ለምን?
3. ሚካኤል የዳንኤል «አለቃ» ነበር።
4. መልሱ ልንረዳቸው በማንችላቸው ምክንያቶች ቢዘገይም እንኳ ጸሎቶች በእግዚአብሔር ይሰማሉ፤ ይመለሳሉም።
5. «በፍታ የለበሰው ሰው» የፋርስንና የግሪክን «አለቆች» መዋጋቱን ይቀጥላል።

አዎን «መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለም፤ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር፥ ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር፥ በሰማያዊም ሥፍራ ካሉ ከክፋት መንፈሳዊያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ»።

ነገር ግን እንድናሸንፋቸው አልተነገረንም። የዲያብሎስን ሽንገላ በመቃወም አቋም እንድንይዝ፥ እንድንጋደል፥ ዲያብሎስን እንድንቃወምና እንድንቆም፥ እንድንጸልይና እንድንነቃ ተነግሮናል። የኤፌ 6 አጠቃላይ አገባቡን ብንመለከተው መከላከልን ይጠቁመናል።

ዓለመቃወም የሚመራን ወደ:-

## መንፈሳዊ ዕውርነትና እሥራት ነው

> «. . . የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዲያበራላቸው የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ» (2 ቆሮ. 4:4)።
>
> «እንግዲህ አሕዛብ ደግሞ በአእምሮአቸው ከንቱነት እንደሚመላለሱ ከእንግዲህ ወዲህ እንዳትመላለሱ . . . እነርሱ ባለማወቃቸው ጠንቅ በልባቸው ደንዳንነት ጠንቅ ልቡናቸው ጨለመ። ከእግዚአብሔርም ሕይወት ራቁ። ደንዝዘውም በመመኘት ርኵሰትን ሁሉ ለማድረግ ራሳቸውን ወደ ሴሰኝነት አሳልፈው ሰጡ» (ኤፌ. 4:17-18)።

እስቲ ይህንን ርዕስ በትክክል ለመገንዘብ ከላይ የተገለጸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በጥሞና ለመመልከት እንሞክር:

1. ‹የዚህ ዓለም አምላክ› ማለትም ሰይጣን የማያምኑትን ሐሳብ አሳውሯል።
2. ይህ ደግሞ የሚያመራው ወደ ጨለመ አዕምሮ ሲሆን፥ ይህም ወደጨለመበትና ወደተደናበረ መንፈሳዊ መረዳት ያደርሳል።
3. የዚህ መንስዔው በሰይጣን ትምህርት ምክንያት ዓይናቸውና ጆሮአቸው መደፈኑ ሲሆን፥ ይህ ደግሞ ልባቸውን ወደ ማደንደን ይመራቸዋል።
4. ዓይናቸውንና ጆሮአቸውን ቢከፍቱ ኖሮ በአዕምሮአቸው ከንቱነት መመላለስ ባላስፈለጋቸውም ነበር፤ ምክንያቱም አላዋቂነታቸው ይወገድ ነበር። የሚገነዘቡና የሚረዱ ይሆኑ ነበር። ልባቸውም ተመልሶ ይፈወሱ ነበር። የሚገነዘቡና የሚረዱ ይሆኑ ነበር። በፈቃደኝነት የሚደረግ ድርጊት አስፈላጊ ነው!

እንዲህ ዓይነቱ መንፈሳዊ ሁኔታ መታሰር ብለን ብንጠራው ትክክል ነው። በእስራት ያሉ ሰዎች እንዴት ነፃ መውጣት ይችላሉ? በዚህ አገባብ መሠረት እስራት ምን እንደሆነ መተርጎም አለብን። ሙስሊሞች ከእስልምና ቢመለሱ ስለሚደርስባቸው ዘላለማዊ ቅጣት እጅግ አድርገው ይፈራሉ። ክርስቲያን ቢሆኑ ሙሉ በሙሉ በቤተሰባቸውና በኅብረተሰቡ እንደሚገለሉ እያሰቡ ይፈራሉ። ከዚህም ጋር አዕምሮአዊና ሥነ-ልቦናዊ ቁስል ይደርስባቸዋል። ከዚህ በተጨማሪ ሙስሊሞች ሞትን እጅግ በጣም ነው የሚፈሩት። በሞቱ ዲያብሎስን ሽሮ ከሞት ፍርሃት ነፃ የሚያወጣውን ኢየሱስን አያውቁትም፤ አያምኑበትምም።

> «. . . በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር:- የሽውም ዲያብሎስ ነው:- በሕይወታቸውም ሁሉ ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት የታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነፃ እንዲያወጣ . . .» (ዕብ. 2:14-15)።

## ከእስራት መፈታትና ነፃ መውጣት

ጌታ ኢየሱስ (በማቴ. 12፡29) ሰይጣንን በ«ኃይለኛ ሰው» ይመስለውና ይህንን አንገብጋቢ ጥያቄን ይጠይቃል፡-

> «ወይስ ሰው አስቀድሞ ኃይለኛውን ሳያስር ወደ ኃይለኛው ቤት ገብቶ ዕቃውን ሊነጥቀው እንዴት ይችላል?» (ማቴ. 12፡29)

ኃይለኛው መጀመሪያ ካልታሰረ በስተቀር በእጁ ያለውን ለመውሰድ አይቻልም። እንግዲህ አሁን የያዛቸውን ማለትም ምርኮኞቹን ለመውሰድ ሰይጣንን ማሰር አለብን ማለት ነው?

ሁላችንም እንደምንስማማው ይህ የተደረገውና መደረግም የነበረበት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ነገር ግን ጌታችን በተደጋጋሚ እኛንም ሆነ ደቀመዛሙርቱን አጋንንትን አውጡ ብሎ አዟል፤ ይህም ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ለእርሱ ስለተሰጠ ነው። በእርሱ ሥልጣን አጋንንትን ማስወጣት እንችላለን፤ አለብንም።

«ሰይጣን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ። እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ የጠላትንም ኃይል ሁሉ ታሸንፉ ዘንድ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፤ የሚጎዳችሁም የለም»። «ኃይለኛውን ማሰር» የሚለውን ስናስብ፥ እነዚያን የጌታ ቃሎች በተጨማሪ እናስባለን፡-

«የመንግሥተ ሰማያትም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ። በምድር የምታስረው ሁሉ በሰማያት የታሰረ ይሆናል። በምድርም የምትፈታው ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል (ማቴ. 16፡19)። እንዲሁም «እውነት እላችኋለሁ የምታስሩት ሁሉ . . .» (ማቴ. 18፡18)።

### ማጠቃለያ

ይህ ሊሆን ቢችልም፤ እኛ ሙስሊሞች በጠቅላላ በርኩስ መንፈስ ተይዘዋል ብለን አናምንም።

እኛ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ምስክሮች እንደመሆናችን መጠን መንፈሳዊው ጦርነታችን ጸሎትን ያካተተ ነው።

1. በጸሎት ይህንን መንፈሳዊ ኃይል ወይም መዋቅር መቃወም እንችላለን፤ ዓላማችንም ሙስሊሞች የተጋረደባቸውን መጋረጃ በመግለጥ፥ ወንጌልን እንዲሰሙና እንዲረዱት፥ በዚሁም እውነተኛ የሆነ የመምረጥ ዕድል እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው።
2. በጸሎት የምንመሰክርባቸውን ሙስሊሞች የሚያጠቃውን ዕውርነትና እስራት ለማስወገድ ጥረት እናደርጋለን።
3. በጸሎት እግዚአብሔርን በሚያስከብርና ለሙስሊሞችም በሚገባቸው መንገድ ለመመስከር ጥረት እናደርጋለን። የምንጸልየውም እግዚአብሔር እኛን እንዲያዘጋጅንና በቃሉና በመንፈስ ቅዱስ እያንዳንዱን ደረጃ እየመራን እንዲጠቀምብን ለማድረግ ነው።
4. በጸሎት፥ በሙስሊሞች መሐል የመንፈስ ቅዱስ መነቃቃት እንዲነሣ

## በእስልምና ያለ የባላጋራነት ግጥሚያ

መንፈሳዊ ጦርነት በአንድ አቅጣጫ ብቻ የሚደረግ አይምሰለን። ባንጻሩ ምናልባት እርግማን ብለን ልንጠራው የምንችለው እንቅስቃሴ አለ።

> በቁርዓን ላይ ስለ ክርስቲያኖች የሚከትለውን እናነባለን:- «አላህ ያጥፋቸው፤ (ከእውነት) እንዴት ይመለሳሉ!» (ሱራ 9:30)። ይህ በሌላ አባባል በጣም ጎልቶ ተገልጿል:-
>
> «እናንተ መጽሐፉን የተሰጣችሁ ሆይ! ፊቶችን ሳናስብና በጀርባዎች ላይ ሳንመልሳቸው ወይም የሰንበትን ባለቤቶች (ያፈረሱትን) እንደረገምን ሳንረግማቸው በፊት ከናንተ ጋር ያለውን የሚያረጋግጥ ሆኖ ባወረድነው (ቁርዓን) እመኑ፤ የአላህም ትዕዛዝ ተፈጻሚ ነው» (ሱራ 4:47)።

የክርስትና ልኡካን በደቡብ ዐረቢያ ከሚገኘው ከናጅራን ወደ መሐመድ ሲመጡ መሐመድ እስልምናን እንዲቀበሉ ግድ አላቸው። እነርሱ ግን እምቢ አሉ። ከዚህ በኋላ የሚከተለው «መገለጥ» መጣለት:-

> «ይህ ከጌታ ዘንድ የሆነ እውነት ነው፤ ከተጠራጣሪዎቹም አትሁኑ፤ ለዕውቀቱም ካመጣልህ በኋላ በእርሱ (በዒሣ) የተከራከሩህን ሰዎች:- ኑ፤ ልጆቻችንና ልጆቻችሁን፤ ሴቶቻችንና ሴቶቻችሁንም ነፍሶቻችንውንና ነፍሶቻችሁንም

እንጥራ፤ ከዚያም አጥብቀን አላህን እንለምን፤ የአላህን ቁጣ በውሸታሞቹ ላይ እናድርግ በላቸው» (ሱራ 3፡60-61)።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እርግማን በእስልምና ውስጥ የሚደረግ ልምምድ ሆነ፤ ዛሬም ሳይቀር ይህ ይደረጋል። (የነዚህ ማስታወሻዎች ጸሐፊ ይህንን ሁለት ጊዜ እንዲያደርግ ተገድዷል። እነዚህ እርግማኖች በክርስቲያን ላይ አይሠሩም። በእርግጥ እንደ ክርስቲያን እኛም መልሰን አንራገምም። እንባርካለን እንጂ!)

# ሠ. ሙስሊሞችን በወንጌል የመድረስ ተግባራዊ ሁኔታዎች

## በቅድሚያ መጤን ያለባቸው ነገሮች

እስካሁን ድረስ ሙስሊሞችን በወንጌል በመድረስ መነሻ ሐሳቦችና መመሪያዎች ላይ ነበር ያተኮርነው፤ አሁን ግን አንዳንድ ተግባራዊ የሆኑ ሐሳቦችንና ፍንጮችን ጨምሮ ጥቃቅን የሆኑትን ነገሮች ሁሉ መመልከት አለብን።

እስቲ ከጅምሩ አንድ ግልጽና ፍጹም የሆነ ዐረፍተ ነገር እንመልከት:-

እግዚአብሔር ሰውን፥ በዚህ ላይ በተለይ ሙስሊምን:- ወደ ራሱ ካልሳበ በስተቀር ምንም ዓይነት ዕውቀት፥ ወይም ችሎታ፥ ምንም ዓይነት ዘዴ፥ ስትራቴጂ ወይም ማንኛውም ዓይነት ብልሃት፥ ምንም ዓይነት መንፈሳዊ ውጤት አይኖረውም:-

«የላከኝ አብ ካሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም. . .» (ዮሐ. 6:44)

መልካሙን የምሥራች እንድናስታውቅ ስለተነገረን ይህንኑ በማድረግ መወሰን አለብን፤ ከዚህም በላይ:- ይህን ስናደርግ ታማኝና ትዕግሥተኛ መሆን አለብን። ጳውሎስ እንዳደረገው ለማሳመን መሞከር፤ ምክንያታዊ በሆኑ መንገዶች በመከራከር ጭምር መጠቀም አለብን። ‹ሁሉን ነገር ለጌታ መተው ነው› በሚባለው የውሸት መንፈሳዊነት ክርስቲያኖች መሰወር የለባቸውም። እስቲ በጥቂቱ እንደገና እንመልከተው:-

«ከግሪክ አገርም መጥተው ከነበሩት አይሁድ ጋር ይነጋገርና ይከራከር ነበር፤ እነርሱ ግን ሊገድሉት ፈለጉ» (ሐዋ. 9:29)።

«ጳውሎስም እንደልማዱ ወደ እነርሱ ገባ። ሦስት ሰንበትም ያህል ከእነርሱ ጋር ከመጻሕፍት እየጠቀሰ ይነጋገር ነበር» (ሐዋ. 17:2)።

«ስለዚህም በሙኩራብ ከአይሁድና እግዚአብሔርን ከሚያመልኩ ሰዎች ጋር በየቀኑም በገበያ ከሚያገኛቸው ጋር ይነጋገር ነበር» (ሐዋ. 17:17)።

«በየሰንበቱም ሁሉ በምኩራብ ይነጋገር ነበር። አይሁድንና የግሪክንም ሰዎች ያስረዳ ነበር» (ሐዋ 12:4)።

«ወደ ኤፌሶንም በደረሱ ጊዜ እነዚያን ከዚያ ተዋቸው። ራሱ ግን ወደ ምኩራብ ገብቶ ከአይሁድ ጋር ይነጋገር ነበር» (ሐዋ. 18:19)።

«ወደ ምኩራብም ገብቶ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት እየተነጋገረና እያስረዳቸው ሦስት ወር ያህል በግልጥ ይናገር ነበር። አንዳንዶች ግን እልከኞች ሆነው በሕዝብ ፊት መንገዱን እየሰደቡ ባላመኑ ጊዜ ከእነርሱ ርቆ ደቀመዛሙርትን ለየ። ጢራኖስም በሚሉት በትምህርት ቤት ዕለት ዕለት ይነጋገር ነበር» (ሐዋ. 19፡8-9)።

ነገር ግን እኛ ስለ ኃጢአት መውቀስ፥ መለወጥ ወይም ማዳን አንችልም። እንድናደርገው የሚጠበቅብንን ነገር በቀላሉ ሳንመለከተው ጥልቀት ባለው የሐላፊነት ስሜት ልንሠራ ይገባል። የሐላፊነት ስሜት ተሰምቶን መሥራት ከፈልግን፥ ራሳችንን በተቻለ መጠን በጥሩ ሁኔታ እናዘጋጃለን። እያንዳንዱ ባለሙያ ዝና የሚያገኘው በመስኩ ስለሠለጠነና የሚያቀርባቸውን ነገሮች በማሳመር ራሱንም እያለማመደ በትጋት ስለሚሠራ ነው። ታዲያ እኛ ምን ያህል ለመማርና ችሎታችንን ለማሻሻል ዘወትር ጉጉት አለን! ወንጌላዊ ‹ሙሉ በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ላይ ማረፍ አለበት› የሚለው መንፈሳዊ የሚመስለው አባባል ራስን ማታለል ነው ብዬ አስባለሁ።

ይህ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስን ምሪት በትጋት መፈለግ የለብንም ማለት አይደለም! ነገር ግን ጳውሎስ፥ ዮሐንስ፥ እስጢፋኖስና ሌሎቹም ቅዱሳን እንዳደረጉትና በመጽሐፍ ቅዱስም እንደምንመለከተው የእኛ ድርሻ የሆነውን «የቤት ሥራችንን» መሥራት አለብን።

ለደቀመዛሙርቱ ጌታ ኢየሱስ ያስተማራቸውን የሚያሳስባቸውና ሁሉን ነገር የሚያስተምራቸው መንፈስ ቅዱስ ነው (ዮሐ 14፤26)። ይህ ማስታወስ ያለብንን ነገር እንዳለ በቅድሚያ ያሳስበናል።

## ጌታ ሆይ እኔ ማን ነኝ?

በውስጣችን የሚፈጠረው መደበኛ የሆነ ጥያቄ፡- እንዲህ ያለ አስቸጋሪ ሥራ ለመሥራት እኔ ማን ነኝ?» የሚል ነው። አንድ ማወቅ ያለብን ነገር ቢኖር ይህንን ጥያቄ ለመጠየቅ እኛ የመጀመሪያዎቹ እንዳልሆንንና እኛ ብቻ እንዳልሆንን ነው!

ሙሴ (ዘጸ. 3፡11 እና 4፡11) እንዲህ ብሏል፡- «ወደ ፈርዖን የምሄድ እኔ ማን ነኝ?» ...እኔ አፌ ኮልታፋ ምላሴም ፀያፍ የሆነ ሰው ነኝ»

ኢሳያስ (ኢሳ. 6፡5) እንዲህ ብሏል፡- «እኔ ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው በመሆኔ ...» ነገር ግን በመቀጠል «እነሆ፥ እኔን ላከኝ!»

ኤርምያስ (ኤር. 1፡6) እንዲህ ብሏል፡- «እኔም ወዮ፥ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ! ብላቴና ነኝና እናገር ዘንድ አላውቅም አልሁ»።

ጳውሎስ (1 ቆሮ. 2፡3)

(2 ቆሮ. 2፡16፤ 3፡5) እንዲህ ብሏል፡- «እኔም በድካምና በፍርሃት በብዙ መንቀጥቀጥ በእናንተ ዘንድ ነበርሁ»። «ለዚህም ነገር የሚበቃ ማነው?» መልሱንም ሲሰጥ፡- «ብቃታችን ከእግዚአብሔር ነው እንጂ በገዛ እጃችን እንደሚሆን አንዳችን እንኳ ልናስብ ራሳችን የበቃን አይደለንም»።

## እስቲ ትክክለኛውን አመለካከት እንፈልግ

ምስክርነታችንን የሚወስኑ ሦስት አመለካከቶች ወይም አስተሳሰቦች አሉ። እነዚህን ማወቅ ትክክለኛ ምርጫ እንድናደርግ ይረዳናል። (በዶ/ር ደብልዩ ባክበርግ በተጻፈው መሠረት ከዮሐ. 18፡28-40 እናቀርበዋለን።)

እንግዲህ እኛ ራሳችንን በተቻለ መጠን በጥሩ ሁኔታ እያዘጋጀን ሳለ ለብቃታችን የእግዚአብሔርን ማኅተም ካላገኘን በስተቀር ዝግጅታችን ያለው ጠቀሜታ ጥቂት ነው። እግዚአብሔርም እንዲህ ብሎ ቃል ገብቷል፡- «እነሆን እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ!»። ነገር ግን እናስተውል፡- ይህ ቃል የተገባው ለሚሄዱ ሰዎች ነው!

1. የመስማማት (የመደራደር) አመለካከት

ጌታችን በጲላጦስ ፊት በጣም በአስከፊ ሁኔታ በነበረበት ጊዜ እንኳ የመስማማት ወይም የመደራደር ነገር አላሳየም። «የተወለድኩት ለዚህ ነው፤ ወደ ዓለም የመጣሁት ለዚህ ነው፥ ለእውነት ልመሰክር መጥቻለሁ» ብሎ ተናገሯል።

በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት እውነት የሚባለው ነገር ከትክክለኛ ዐረፍተ ነገር በጣም የላቀ ይዘት አለው። ይህንንም ስንል ትክክለኛ ዐረፍተ ነገር በሐሳብ፥ በሳይንስና በተጨባጭ ሁኔታዎች መሠረት እውነት ሊሆን ይችላል። እንዲያውም በመጠይቃዊ አገላለጽ (ሎጂካሊ) አሳማን ሆና የመጽሐፍ ቅዱስን የእውነት መመዘኛ ላያሟላ ይችላል።

ስለዚህ አንድ የክርስቶስ ምስክር በመጽሐፍ ቅዱስ መመዘኛ መሠረት እውነት ያልሆነውን እውነት ነው ብሎ ቢናገር፥ ክርስቶስ የተቃወመውን የመስማማት አመለካከት መቀበሉ ስለሆነ በደለኛ ይሆናል።

## 2. የመዝሙት አመለካከት

ኢየሱስ እንዲህ ብሏል:- «መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም፤ መንግሥቴ ከዚህ ዓለም ብትሆን ኖሮ ሎሌዎች ይዋጉልኝ ነበር ...»። በመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ላይ የተቀመጠው በጣም አስደሳች የለዋሰው አጠቃቀም ይህን ክፍል እንድንረዳው ይረዳናል። ይህም በግሪክ ምንባብ ውስጥ ሁኔታን በሚገልጸው ሐረግ «ይዋጉልኝ ነበር» በሚሉ ቃላት ላይ ያርፋል። ዶ/ር ባክበርግ ሲጽፍ:-

«በግሪክ ሁለት ዓይነት ሁኔታ አመልካች ሐረጎች አሉን» ብለዋል። ሀ) ገሃዳዊ ወይም ክፍት ሁኔታዎች፥ ለምሳሌ:- ‹እሑድ አየሩ ተስማሚ ከሆነ፥ በጸሐይ ላይ ተቀምጠን ቁርሳችንን እንበላለን» ይህ እውነተኛና ክፍት ነው፤ ሊሆን የሚችል ነገር ነው።

ለ) ነገር ግን:- «ክንፎች ቢኖሩኝ ኖሮ፥ ዛሬ ከሰዓት በኋላ ሴት ልጄንና የልጅ ልጆቼን በአስቸኳይ እጎበኛቸው ነበር» ብል፥ ሁኔታው ከእውነት የራቀ ነው። እዚህ ላይ ሁለቱም ማለትም ሁኔታው (ክንፎች አሉኝ) እና ክስተቱ (ልጄን እጎበኛለሁ) ሊጠየቁ የማይችሉ መሆናቸውን ልብ ልንል ይገባል።

በዮሐንስ 18፡36 የተጠቀሰው ሁኔታን የሚገልጸው ዐረፍተ ነገር ከእውነት የራቀን ክስተት የሚያሳይ ነው። «መንግሥቴስ ከዚህ ዓለም ብትሆን፥ ሎሌዎቼ ይዋጉልኝ ነበር»። በጌታችን በእነዚህ ቃላት «የመንግሥቱ የዚህ ዓለም መሆንና» «የሎሌዎቼም መዋጋት» ጨርሶ ሊሆን የማይችል መሆኑን ይገልጻል።

የመጀመሪያዎቹ የመስቀል ዘማቾች በሰይፎችና በጦሮች መዋጋታቸው በክርስቲያኖች ሁሉ ዘንድ የተጠላና የተወገዘ ቢሆንም፤ እኛም ሙስሊሞችን ለመፋለም በምንጥርበት ወቅት የመስቀሉ ዘማች አስተሳሰብ ሊኖረን ይችላል። ይህም አመለካከታችን ወደማያስፈልግ ፍጥጫ እንደሚመራ ጥርጥር የለውም። ይሁን እንጂ ሊወገድ የማይችል ፍጥጫ እንዳለም ልናስተውል ይገባል። ይኸውም እውነት በሆነውና ባልሆነው መካከል ያለው ዓለመግባባት ነው።

## 3. ሚሲዮናዊ አመለካከት

እዚህ ላይ ጌታችን እንደ ወንጀለኛ በከፍተኛ ዳኛ መስቀለኛ ጥያቄ እየተጠየቀ መሆኑን ልናስታውስ ይገባል። ዳኛው ጥፋተኛ መሆን ዓለመሆኑን ይጠይቃል:- «የአይሁድ ንጉሥ አንተ ነህን?» ከዚያም ያልተጠበቀና ለማድመጥም የሚከብድ ነገር ተፈጠረ። ተከሳሹ ጥያቄውን በጥያቄ መለሰ። «አንተ ይህን የምትለው ከራስህ ነውን ወይስ ሌሎች ስለ እኔ ነገሩህ?» አለው። ይህ ፈራጁን ማቃለል አይደለምን? ጌታችን ለምን ይህን ጥያቄ በጥያቄ መለሰ?

በዚህ ጊዜ ጌታችን የእርሱና የጲላጦስ ሚና የሚቀያየርበት ቀን አስቀድሞ እንደተመለከተ አምናለሁ። እርሱ ፈራጅ ሆኖ ሲቀመጥ፥ ጲላጦስ ተከሳሽ ሆኖ የሚቀርብበትን ቀን ማለት ነው። እርሱ ለጲላጦስ ኃጢአቶችም ደግሞ ዋጋ በመክፈል ሂደት ውስጥ ነበረ። «ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምፄን ይሰማል» በሚልበት ጊዜ፥ ይህ እርሱንም እንደሚጨምር ጲላጦስ በግልጽ ተረድቷል። ጲላጦስ በዚህ ጥያቄ ላይ ለምን ያህል ጊዜ እንዳሰበ አናውቅም። የምናውቀው ነገር ቢኖር ወደ ጎን ገሸሽ አድርጎት ወደ ፍልስፍናው መሥመር እንደሸሸ ብቻ ነው። ትክሻውን በመስበቅና «እውነት ምንድር ነው?» የሚለውን ለዘብተኛ ጥያቄ በመጠየቅ ወጥቶ ሄደ። በዚህም በዘላለም ዕድሉ ላይ አተመበት።

ጌታችን ግን እስከመጨረሻው እስትንፋሱ ድረስ ነፍስ ማራኪ መሆኑን አሳይቷል ሚሲዮናዊ አስተሳሰቡ የደጎነነት ሥራው እምብርት ነበር።

እስኪ ራሳችንን እንመርምር

አገልግሎት መንፈሳዊ ውጊያ ነው። በመንፈሳዊ ማታለሎችና ውሸቶች ላይ የሚነሣ ጥቃት ነው። ስለዚህም የእግዚአብሔርን የጦር ዕቃ ሁሉ ልንለብስ ያሻናል።

እነዚህን ጉዳዮች በምንመለከትበት ጊዜ እያንዳንዳችን ልባችንን መመርመር አለብን።

ለጌታዬ ያለኝ አመለካከት ምንድነው?

ለእርሱ ተሰጥቻለሁ?

ቃሉን በሙሉ ልቤ አምኜ እታዘዛለሁ?

ታላቁ ተልዕኮ እኔን እንደሚመለከተኝ አድርጌ ተቀብያለሁ?

የእኔ ፈቃድ በፍቅር ለእርሱ ፈቃድ ተገዝቷልን?

ስለጠፉት ሙስሊሞች የእኔ አመለካከት ምንድነው?

አክብሮት ነው? ፍቅር ነው? አንድነትና ኅብረት ነው?

ጥርጣሬና ዓለመታመን ነው? ፍርሃት ነው? ግዴለሽነት ነው?

ሙስሊሙ ጠላቴ ነውን?

የእግዚአብሔር ፍጥረት እንደሆነና፥ በእርሱም መወደዱን፥ ዳሩ ግን ወደ ስሕተት እንደተመራ አድርጌ ነው የምቆጥረው?

ወይስ ለሃይማኖቱ የተሰጠና ታማኝ ሆኖ ሳለ ኢየሱስንና ሥራውን ግን በይበልጥ ማወቅ የሚያስፈልገው ወንድሜ ነው? ወይስ በጋራ መተማመን፥ በፍቅርና በመረዳዳት የተሻለ ዓለም ለመፍጠር አብረን መሥራት አለብን?

ስለ እስልምና ያለኝ አመለካከት ምንድነው?

እስልምና የተሰጡና ታማኝ የሆኑ አማኞች የሚገኙበት በአንድ አምላክ የሚያምን ሃይማኖት ነው? ወይስ ሌላውን ኢየሱስ በተለየ መንፈስ የሚሰብክ ሌላ ወንጌል ነው?

እስልምና ለእኔ የታወቀ የመስቀል፥ የደኅንነት፥ የስርየትና የክርስቶስ ጸጋ ጠላትና በዚያውም ፀረ-ክርስቲያን ነው? ስለዚህ አንዳች ነገር ለማድረግ ተዘጋጅቻለሁን?

የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት በሚያስፈልጉ ተገቢ መሣሪያዎች ላይ ያለኝ አመለካከት ምንድነው?

በበለጠ ለመታጠቅ ነገሮችን ማስቀደምን በቋሚ ሁኔታ ስል ለመጣር ፈቃደኛ ነኝን? ትክክለኞቹን እፈልጋለሁን?

> አመለካከታችን ግንኙነታችንንና ከአንድ ሙስሊም ጋር
> ወንጌሉን በእውነተኛ መንገድ ለመካፈል
> የምናደርገውን ጥረት ውጤት ይወስነዋል።

## ችሎታዎች

ምንም እንኳ ፈቃደኛ ልብ ያለውን ሰው ለሙስሊሞች ወንጌል ከማዳረሱ አገልግሎቶች ወደኋላ እንዲል ባንገፋፋም፥ መስካሪው ሊኖረው የሚገቡ ስጦታዎች ወይምን ችሎታዎችን መመልከት አለብን።

ይህ ባመዛኙ በሁኔታውና በተካፋይነቱ መጠን ይወሰናል። በክልል ደረጃ እያንዳንዱ ክርስቲያን ጎረቤቱ ወይም የሥራ ባልደረባው ለሆነው ወይም ለሆነችው ሙስሊም ለመመስከር መቻል አለበት። ይህም ቢሆን ዝግጅት በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ለማሳሰብ እንሻለን። በመሠረታዊ ጉዳዮችም ላይ ቢሆን ማለት ነው።

በሙስሊም የወንጌል ሥርጭት ለመካፈል የሚፈልጉ ሁሉ ችሎታቸውን ለማሳደግና ስጦታቸውንም ለማጎልበት መጣር እንዳለባቸው እንመክራለን። ይሁንና ከዋንኛ ነገሮቹ አብዛኛዎቹ ለሁሉም ክርስቲያን ተፈጥሮአዊ መሆን ይገባቸዋል፡-

* ርኅራኄ፡- ምንም ዓይነት የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት ወይም ትምህርት በማይሰጥበት መዋቅር ውስጥ ተታለው ያለ አዳኝ ለሚኖሩ ወንዶችና ሴቶች መራራት ያሻል። ምንም እንኳ ቀናተኛና ታማኝ ሰዎች ቢሆኑም ጠፍተዋል፡-

«በዕውቀት አይቅኑ እንጂ ለእግዚአብሔር እንዲቀኑ እመሰክርላቸዋለሁና። የእግዚአብሔርን ጽድቅ ሳያውቁ የራሳቸውን ጽድቅ ሊያቆሙ ሲፈልጉ፥ ለእግዚአብሔር ጽድቅ አልተገዙም» (ሮሜ 10፡2-3)።

ይህም ጽድቅ በእምነት የሚገኝና ክርስቶስ ኢየሱስ በሠራው ሥራ ላይ የተመሠረተ ነው። ለሙስሊም በጥሩ ሁኔታ የሚስማማ እንዲህ ያለ ምንባብ የለም።

* የሌላውን ሰው ስሜት መጋራት፡- የሌላውን ስሜት ለመረዳት ፍላጎት ከሌለን በትክክል ለመግባባት ያስቸግረናል። በተለይም ከሌላ ሃይማኖት ተከታይ ጋር ሲሆን ይህ ወሳኝ ነው፡-

«ከሰው ሁሉ አርነት የወጣሁ ሲሆን የሚበልጡትን እንድጠቅም እንደ ባሪያ ራሴን ለሁሉ አስገዛለሁ። አይሁድንም እጠቅም ዘንድ ከአይሁድ ጋር እንደ አይሁዳዊ ሆንሁ፤ ከሕግ በታች ያሉትንም እጠቅም ዘንድ እኔ ራሴ ከሕግ በታች ሳልሆን፥ ከሕግ በታች ላሉት ከሕግ በታች እንዳለሁ ሆንሁ፤ ሕግ የሌላቸውን እጠቅም ዘንድ፥ ያለ እግዚአብሔር ሕግ ሳልኖር፥ ነገር ግን በክርስቶስ ሕግ በታች ሳለሁ፥ ሕግ ለሌላቸው ሕግ እንደሌለኝ ሆንሁ፤ ደካሞችንም እጠቅም ዘንድ፥ ለደካሞች እንደ ደካማ ሆንሁ፤ በሁሉ መንገድ አንዳንዶችን አድን ዘንድ፥ ከሁሉ ጋር በሁሉ ነገር እንደ እነርሱ ሆንሁ። በወንጌልም ማኅበርተኛ እሆን ዘንድ ስለ ወንጌል ሁሉን አደርጋለሁ» (1 ቆሮ. 9፡19-23)።

* አስቸጋሪውን አሳብ በቀላልና ለሰዎች ሊገቡ በሚችሉባቸው መንገዶች አቀናጅቶ የማስተላለፍ ብቃት፡-

«እኛ ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ እንዲያ የተሰጠንን እናውቅ ዘንድ ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ የዓለምን መንፈስ አልተቀበልንም። መንፈሳዊውን ነገር ከመንፈሳዊ ነገር ጋር አስተያይተን መንፈስ በሚያስተምረን ቃል ይህን ደግሞ እንናገራለን እንጂ የሰው ጥበብ በሚያስተምረን ቃል አይደለም» (1 ቆሮ. 2፡12-13)

* ድፍረት፡- ሌሎች ስለመሄድ እግራቸው የሚሰበስቡባቸው ሥፍራዎች በመሄድ አስቸጋሪ ሁኔታዎች እንኳ ቢኖሩ፥ እምነትን በፍቅር ለማካፈል መድፈር፡-

«እኛ ግን ነፍሳቸውን ሊያድኑ ከሚያምኑ ነን እንጂ ወደ ጥፋት ከሚያፈገፍጉ አይደለንም» (ዕብ. 10፡39)

* ትሕትና:- ሙስሊሙን ወይም ሙስሊሟን ማናናቅ ሳይሆን በእኩልነት መንፈስ ማነጋገር ይገባል:-

«አንተ እንድትበልጥ ማን አድርጎሃል? ያልተቀበልኸውስ ምን አለህ? (1 ቆሮ. 4:7)።

«እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ የእምነትን መጠን እንደከፈለው እንደ ባለ አእምሮ እንዲያስብ እንጂ ማሰብ ከሚገባው አልፎ በትዕቢት እንዳያስብ በመካከላችሁ ላለው ለእያንዳንዱ በተሰጠኝ ጸጋ እናገራለሁ» (ሮሜ 12:3)

«ደስታዬን ፈጽሙልኝ፤ በአንድ አሳብ ተስማሙ፤ አንድ ፍቅር፥ አንድም ልብ፥ አንድም አሳብ ይሁንላችሁ፤ ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንኳ አታድርጉ፤ ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቁጠር» (ፊልጵ. 2:2-3)።

* መታመን:-

«እንዲሁም ሰውም እኛን እንደ ክርስቶስ ሎሌዎችና እንደ እግዚአብሔር ምስጢር መጋቢዎች ይቁጠረን። እንዲህም ሲሆን፥ በመጋቢዎች ዘንድ የታመነ ሆኖ መገኘት ያስፈልጋል» (1 ቆሮ. 4:1-2)።

በሙስሊም የወንጌል ሥርጭት ውስጥ በጣም የሚጎድለው ባሕርይ ምናልባት መጽናት ይሆናል።

* የተጋጋሉ ጉዳዮች ላይ ባለመረበሽ በእርጋታ የመከራከር ችሎታ:- ይህ የትምህርቱን ዕውቀት፥ ባመዛኙ ይቅርታ ጠያቂነትንና ቁጥብነትን ከመጠየቁም በላይ ጉዳዮችን በመገምገም በፍቅር ግልጽ የማድረግን ችሎታ ያሻል።

«ስለዚህ የልቡናችሁን ወገብ ታጥቃችሁና በመጠን ኖራችሁ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ የምታገኙትን ጸጋ ፈጽማችሁ ተስፋ አድርጉ» (1 ጴጥ. 1:13)።

«በመጠን ኑሩ፤ ንቁም፤ ባለጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና» (1 ጴጥ. 5:8)።

* ለመጸለይ መፍቀድ።

ከሚያሳውሩና ከሚያስሩ ሥልጣናት ጋር ለምናደርገው ትግል ቁልፉ ጸሎት ነው (ኤፌ. 6:10-20)

## ዝግጅትና ልምድ

ቀደም ብሎ ዝግጅትና መረዳት፥ ጸሎትና ልምድ ጎን ለጎን እንደሚሄዱና ማናቸውም ለሌላው ምትክ እንደማይሆኑ ተገልጿል። ደግሞም አንድ ሰው ራሱን

ለሙስሊም የወንጌል አገልግሎት እስካልሰጠ ድረስ ልምዱ ለማግኘት እንደማይችል ግልጽ ነው። እንዲሁም ዝግጅት በሙስሊም የወንጌል ሥርጭት ላይ የተጻፈ መጽሐፍ በማንበብ፥ ወይም በዚህ መስክ አንዱ ሴሚናር በመካፈል የሚያበቃ ነገር አይደለም።

እኛ ወንጌሉን ለማስተላለፍ ስጦታ ይኑረው አይኑረው በረዥም ልምምድ ፈትኖ እስካልደረሰበት ድረስ ለማወቅ አይችልም። ትምህርት እስካልተሰጠውና በርካታ የልምምድና የጥናት ሰዓቶች እስካልወሰደ ድረስ፥ ማንም ሰው ፒያኖ ለመጫወት፥ ስጦታው ይኑረው ወይም አይኑረው ለማወቅ አይችልም ችሎታ የሚመጣው ከትምህርትና ከልምድ ነው። ይህ ደግሞ የስሕተቶችን መከሰት አያግድም። እያንዳንዱ መስካሪ ከእነዚህ ስሕተቶች ለመማርና ደግሞም ላለመሥራት መጣር እንዳለበት ሊያምን ይገባል።

አስፈላጊ ቢሆን እንኳ፥ ከመጻሕፍት ወይም ከክፍለ ትምህርት የምንማረው ነገር በፍጹም ልምድን ሊተካው አይችልም። በሌላ በኩል ደግሞ ልምዱ ያለ ትምህርት ወደ ዕውቀትና ውጤታማ ግንኙነት መምራቱ በጣም አጠራጣሪ ነው። ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «ትንቢትም ቢኖረኝ፥ ምስጢርንም ሁሉና ዕውቀትንም ሁሉ ባውቅ፥ ተራሮችንም እስከማፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ፥ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ» (1 ቆሮ. 13፡2) እንደተባለ እናውቀለን። ይህም በሌሎች ግሩም ቃላት ታጅቧል፡- «ፍቅር ይታገሣል፤ ቸርነትንም ያደርጋል «ፍቅር አይመካም፤ አይታበይም፤ የማይገባውን አያደርግም፤ የራሱንም አይፈልግም፤ አይበሳጭም፤ በደልን አይቆጥርም፤ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፤ ሁሉን ይታገሣል ሁሉን ያምናል፥ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል በሁሉ ይጸናል። ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም»። ይህም በምዕራፍ 8፡1 በጥሩ ሁኔታ ዳብሯል፡- «ዕውቀት ያስታብያል፤ ፍቅር ግን ያንጻል»። ይህ ግን ዕውቀትን መፈለግ የለብንም ማለት ሳይሆን፥ ትሕትናን መሻት ይገባናል ማለት ነው።

## ተግባራዊና ባህላዊ ግምገማዎች

ወንጌል ከባህል የላቀ መሆኑን መስካሪው ልብ ሊል ይገባል። ወንጌልን ለመረዳት፥ ለመቀበልና ለመከተል ማንም ሰው ባህሉን መለወጥ አያስፈልገውም። በመሠረቱ ውስጥ መገለጽ አለበት። ነገር ግን እነዚህ ሌላው የባህል አባላት መሰናክል መሆን የለባቸውም። መጽሐፍ ቅዱሳዊውን እምነት ይዘት በተመለከተ ምንም ዓይነት ማካካሻ ሊደረግ ባይቻልም እንኳ የእኛን ባህላዊ ገጽታዎች ግን በሌላው ላይ የምንጭንበት ሥልጣን የለንም። በቅርፅና በይዘት መካከል ያለውን ልዩነት በግልጽ ማውጣቱ ጥበብን፥ ችሎታንና ዕውቀትን ይጠይቃል። ዳሩ ግን አሁን ያለው ወይም

የቀደመው ሃይማኖት በባህል ላይ ያስከተለውን ውጤት መረዳት አለብን። ችግሩ እኛ ባህላዊ ገጽታዎች ናቸው የምንላቸው ነገሮች የእስልምና ይዘት ያላቸው እስላማዊ ምልክቶች ሊሆኑ ይችላሉ። ወደ ቤተክርስቲያን እንዲመጣ ከፈቀድን ግን ሁለት ተቃራኒ ነገሮችን ጎን ለጎን የማስኬዱ አደጋ የማይቀር ነው። እያንዳንዱን የክልሉን ሁኔታዎች በጥንቃቄ በመመርመርና በንቃት መከታተል ምን መደረግ ወይም መባል እንዳለበትና እንደሌለበት ማወቅ ያስፈልጋል።

አላህ፥ ቁርዓን፥ እስልምናና መሐመድ በሙስሊሙ ዘንድ የማይነኩ ተብለው ሊጠሩ የሚችሉ ነገሮች ናቸው። በሙስሊም መሪዎች ላይ ሂስ ማቅረብ የተወሰኑ ልምምዶችን ወይም አንድን የፖለቲካ አርምጃን በሚመለከት ከሙስሊሞች ጋር ያለችግር ለመወያየት ይቻላል። ዳሩ ግን፥ የማይነኩትን መንካት ጫን ያለ ተቃውሞ የሚያስከትል ይሆናል።

በሌላ በኩል በአንድ ወይም በሌላ ጊዜ ስለ እነዚህ ነገሮች ከመከራከር መቆጠቡ አስቸጋሪ ነው የሚሆነው። አሊያም መሠረታዊ ጉዳዮቹን ማወዳደሩ አቀበት ይሆናል። ሙስሊሞች አሉታዊ የሆነውን ነገር በመሰወርና አዎንታዊ የሆነውን ነገር በስፋት በማስተዋወቅ ስለ እስልምና በጣም ውሱን ግንዛቤ አላቸው። ይህም ቢሆን ባመዛኙ አሳባዊና ሐቅን ያልተመረኮዘ የእስልምና ገፅታ ነው።

«ስለ እስልምና ምን ታስባለህ?» በማይነኩት ነገሮች ላይ ያለንን አመለካከት ብንጠይቅ ምን ምላሽ እንሰጣለን? ሙስሊሞች አንድም አዎንታዊ፥ ካልሆነም ያላዋቂነትን ምላሽ በመጠበቅና እስልምናን ለማስፋፋት ሲሉ እንዲህ ዓይነት ጥያ ቄ ይጠይቃሉ። እኔ ሁልጊዜም ጥያቄውን መገልበጡ ከሁሉም የተሻለ ሆኖ አግኝቻለሁ፡- «ስለ መሐመድ /እስልምና/ ቁርዓን የማስበውን ነው? መልካም፤ እኔ ክርስቲያን ነኝና እኛ ካለን ጋር አወዳድራለሁ። እስልምና ትክክለኛ መንገድ መሆኑንና በእግዚአብሔርም ዘንድ ተቀባይነት እንደሚኖረው ባምን ኖሮ ሙስሊም እንጂ ክርስቲያን አልሆንም ነበር። እስካሁን ግንም ያሳመነኝ የለም። አየህ፥ እኛ በመጽሐፍ ቅዱስ እናምናለን። በዚያም ውስጥ ለተአማኝነቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዋስትና የሌለውን ማንኛውንም መልዕክት እንዳንቀበል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶናል። ይኸውም የተፈጸመ ትንቢት ነው (ዘዳግም 18፡21-22፤ ዘካርያስ 4፡9፤ ኢሳይያስ 41፡21፤ 44፡7፥26 አሞጽ 3፡7፤ ኤርምያስ 28፡9፤ ዘዳግም 13፡1-4 ወዘተ)። እስኪ ምሳሌ ልስጥህ። እዚህ ላይ ለሙስሊሙ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ኢየሱስ፥ ምን እንደሚያደርግና እንዴት እንደሚሞት የሚናገሩትን ማሳየት እንችላለን፤ («የእስልምናና የክርስትና ግጭቶች» ገጽ 36-49 ተመልከት)። ከዚያም ቁርዓን የክርስቶስን መምጣት ዋና ዓላማ እንደሚቃረን ማሳየታችንን መቀጠል እንችላለን፡- ይኸውም እኛን ከአብ አባቱ ጋር ለማስታረቅ በመስቀል ላይ መሞቱን ነው።

«የትኛውን እንድቀበል ትፈልጋለህ፡- ለብዙ መቶ ዓመታት በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ነቢያት በብዙ ዝርዝር የተነበዩትን፥ በታላቅ ትክክለኛነት የተፈጸመውን፥ በወንጌል ውስጥ በአራት የተለያዩ ምስክሮች የተዘገበውን፥ ዘላለማዊው ሕይወታቸው በእውነተኛነታቸው ላይ በተመሠረተ የዓይን ምስክሮች የተጠናከረውንና በታሪክና በክርስ-ምድር ምርምርም የተደገፈውን ወይስ ከ600 ዓመታት በኋላ ምንም ትንቢት በሌለበት መጽሐፍ ውስጥ አንድ ሰው የጻፈውን?»

በመጠኑ ሐቀኛ የሆነ ማንም ሰው በዚያ ላይ ጥያቄ ያቀርብልንና ዕድሉን በደስታ ለምስክርነት እንጠቀምበታለን፥ ወይም የተባለውን ሁሉ ይቀበላል። ሆኖም፥ አቅጣጫቸውን በመቀየር አብዛኛዎቹ ሙስሊሞች ከመከራከሪያ ነጥቦቻቸው ውስጥ አንዱን በማንሣት ይደራደራሉ። እነዚህም እንደ፡- መጽሐፍ ቅዱስ ተለውጦ ተበላሽቷል! ወይም ኢየሱስ እንዴት አምላክ ይሆናል ወዘተ ያሉት ናቸው። እዚህጋ ብልሆች በመሆን ያንን ክርክር ወደ ዋናው ቁም ነገር መልሰን ለማምጣት መቻል አለብን። እውነቱን ማጽናት አለብን። ኢየሱስ ተሰቅሎ ሞቷል ወይስ አልሞተም? ደግመህ ወደ መረጃው ተመልከትና በታማኝነት ተናገር።

ሙስሊሞች እንዲህ ካለው አቀራረብ ጋር አልተላመዱም።

ሁልጊዜም የምትለውን ነገር ለማጠናከር ተዘጋጅ። ግላዊ እምነቶቻችንና አመለካከቶች ምንም ጠቀሜታ የላቸውም። በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በታሪክ፥ ወይም በእስልምና ላይ አንድ መግለጫ ስንሰጥ ምንጮችን፥ ጉዳዩን በግልጽ ማቅረባችንና ትክክለኛ የጥቅሶችን ምንጭ መስጠታችንን ማረጋገጥ አለብን። ይህ ምናልባት ወዲያውኑ የማይቻል ቢሆን፥ በሚቀጥለው ቀጠሮ ወይም ቀን ማቅረብ እንችላለን። ሁልጊዜም የነጥብህን እውነተኛነት ለማረጋገጥ ዓልም። ደግሞም ለቆመለት ነገር ማረጋገጫ ማቅረብ ብዙም ከማይሆንለት ሙስሊም ጓደኛህ ይህንን ተጠባበቅ። በተለይም ስለ እስልምና በበቂ ሁኔታ ተረድተን ስንቀርብ የሚያቀርብልን ተጨባጭ ማረጋገጫ አይኖረውም።

ማዕረጎችንና ስሞችን በጥንቃቄ መጠቆም ያስፈልጋል። እስኪ ተመልከት ከልባችን ‹ነብዩ መሐመድ› እያልን ለመናገር እንችላለን? ደግሞስ ለሙስሊም (ወይም ለሌላ ክርስቲያን ላልሆነ ሰው) ‹ጌታ ኢየሱስ› እያልን እንናገራለን? ለእኛ መሐመድ ነቢይ አይደለም፥ ለሙስሊሞች ደግሞ ኢየሱስ በፍጹም ጌታ አይደለም። ስለዚህ በዚህ ረገድም ቢሆን በውይይታችን ውስጥ ልንነቃና እውነተኞች ልንሆን ያሻል። ኢየሱስን ጌታ ብዬ ለሙስሊሞች አልናገርም። ይልቁንም መሢሑ ኢየሱስ ብዬ እጠራዋለሁ።

የወንድና የሴት ግንኙነቶች በእስልምና ከምዕራባውያን በበለጠ ጥርጣሬ፥ በግትርነትና በትኩረት ይታያሉ። ስለዚህ አንድ መስካሪ ባልተፈቀደ ጉዳይ ውስጥ እንዳልገባ እርግጠኛ መሆን አለበት። ለእኛ ተራ ጭውውት የሆነው ነገር በእስልምና አግባብ እንደሌለውና እንዲያውም እንደ ጥቃት የሚወሰድ ሊሆን ይችላል። በተለይ ከሰላት ወይም ናማዓዝ ጸሎት በፊት ከሚሆን የመተጣጠብ መረዳት በኋላ እጅ መጨባበጥ እንኳ እንደመርከስ ሆኖ ሊቆጠር ይችላል። አንድ ሰው ተቃራኒ ፆታ ካለው/ላት ሰው ጋር ለብቻው/ለብቻዋ በመወያየት እንዳያጋልጠው/ጣት መጠንቀቅ አለበት።

አለባበስ:- በእስልምናው ዓለም አስፈላጊነቱ እየጨመረ የመጣ ገፅታ ነው። ከጊዜ ወደ ጊዜ ብዙውን የሰውነት ክፍላቸውን በማይማርኩ ልብሶች እየሸፈኑት መጥተዋል። ይህም በሌሎች በርካታ መንገዶች ሊገለጽ የሚችለውን ሌላውን የመማረክን ነገር ለማስቀረት ለሚደረገው ጥረት ሲባል የሚፈጸም የጨዋነት ምልክት መሆኑ ነው። በእስልምና ውስጥ ያለውን የተለየ የጨዋነትን ወይም ግብረ ገብን ግንዛቤ መረዳት አለብን። በመጀመሪያና አሁንም ቢሆን በሺሃ ቡድኖች አካባቢ «ሙታህ» ማለትም ለጥቂት ሰዓታት፥ ወይም ቀናት፥ ወይም ሳምንታት የሚሆን ጊዜያዊ ጋብቻ እየተፈጸመ እንኳ የሚጋቡት ወጣቶች አዋቂ ሴት አብራቸው ሳትኖር ብቻቸውን በፍጹም እንዳይገናኙ የሚያግዳቸው ልምድ አሁንም አስፈላጊ ሆኖ ይሠራል።

በአንዳንድ ባህሎች ‹ቡርካ› ማለትም የዓይን ርግብ መጠቀምንም ጨምሮ ሰውነትን ሁሉ መሸፋፈን ወንዶችን ላለመሳብ ሲባል የሚደረግ ነው። ለክርስቲያኖች እንደነዚህ ዓይነት ልምዶችን መረዳት አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም እኛ ጨዋነትንና ግብረገባዊነትን መለማመድ ያለብን ከልባችን እንጂ አጋጣሚው ስላላመቸን አይደለም። እንዲሁም ክርስቶስን ከማፍቀርና በማክበር የተነሣ ከሚስታችን ወይም ከባላችን ጋር የተለየ ዓይነት ግንኙነት አለን።

መሰናከል ላለመሆን ከሙስሊሞች ጋር ግንኙነት ያላት ክርስቲያን ሴት ራሷን የወንዶችን ምኞት የማይቀሰቅስና የባህሉን መመዘኛ የማይጻረር ዓይነት አለባበስ ትመርጣለች። ትከሻን የሚሸፍን፥ እጅጌ-ጉርድ አንገትን የማያጋልጥና ጥሩ ርዝመት ያለው ልብስ በብዙ ሁኔታዎች ተቀባይነት አለው። በሌላ በኩል ደግሞ ለማታለል ብሎ አለባበሳቸውን እንደለበሰ ተደርጎ እንዳይወነጀል መጠንቀቅ ያሻል። የምናውቃቸው ሚሲዮናውያን የባህል ልብስ በመልበሳቸው እንዲህ ዓይነት ዕድል ገጥሞአቸዋል።

የራስን ሕጎች በሌላው ላይ ባለመጫን፥ ጠለቅ አድርጎ መመልከትና ብልሃተኛ መሆን እያንዳንዱ ምስክርነት በትክክለኛ መሥመር እንዲሄድ ያደርጋል።

ቀኝ እጅ ለ «ንጹሕ» ተግባራት ለምሳሌም እንደ መብላት ላለ አገልግሎት ሲውል፣ ግራ እጅ ደግሞ «ንጹሕ ላልሆኑ» ሽንት ቤት ከተጠቀሙ በኋላ እንደ መጸዳዳት ላሉ ተግባራት ያገለግላል። ይህ ግራ እጁን በመጠኑም ቢሆን ዝቅ ያደርገዋል። በብዙ የምሥራቃውያን ባህሎች ግራ እጅ ከገበታም በታች ሲደረግ፣ የመብላት ሂደቱ በቀኝ እጅ ብቻ ይቀለጣጠፋል። ብዙውን ጊዜ ምሥራቃውያን በመስተንግዶአቸው ላይ ምዕራባውያን የሚመገቡባቸውን ዕቃዎች የሚቀርቡ መሆናቸው የታወቀ ቢሆንም፣ ይህ ካልሆነ ግን መስካሪው ለመብላት ቀን እጁን እንዲጠቀም እንመክረዋለን።

እንግዳ ተቀባይነት በብዙ ምሥራቃውያን ዘንድ እጅግ ከፍተኛ ዋጋ አለው። በእርግጥ ለሙስሊሞችም እንዲሁ ነው። ይህን አልቀበልም ማለት አስከፊ ነገር ሊሆን ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ ጋባዡ ሙስሊሞቹ ሳይፈልጉ ካልጋበዝኩ ብሎ ችክ ማለት የለበትም። ላለመፈለጋቸው ይኸውም በቂ ምክንያት አላቸው:-

የሐላል ሕግ። በእስልምና ባሕርይና ማንኛውም እንቅስቃሴ በሁለት ክፍል ተከፍ»ል:-ሕጋዊና ሕገ-ወጥ። ደብልዩ ኤች. ገይርድነር የዚህን መሠረት ያብራራዋል:- «የተወሰኑ ነገሮችን ትክክል፥ ሌሎች የተወሰኑትን ደግሞ ስሕተት አድርጎ የሚመድባቸው ትእዛዝ በአብዛኛው ከአስተዳደር ሥራ ባህርይ ጋር የሚወገን ነው:- «ትክክል» ወይም «ስሕተት»፥ «የተፈቀዱ» (ሐላል) ወይም «ያልተፈቀዱ» (ሐራም) (ነውር!) አድርጎ አይፈጥራቸውም። በራሳቸው የሚያስጠሉ ሳይሆኑ፥ ዳሩ ግን የፍጹሙ ሱልጣን ትዕዛዝ መፈጸሚያዎች ናቸው» («የእስልምና ተግዳጽ»)።

የምግብ ሕግጋትም በዚህ ሥርዓት ውስጥ ተጠቃልለዋል። ለእኔ እንደሚገባኝ፥ በአይሁዳዊ ኮሸር ሕግም ሆነ የሐላል ሕግጋት ከመጀመሪያው ዓላማና ዕቅድ ርቀው ሂደዋል። በመሠረቱ አንድ ሙስሊም እንዲበላው የተፈቀደለት በእስልምና ሥርዓት መሠረት አንገቱ ተቆርጦ እስኪሞት ድረስ ደሙ የፈሰሰ እንስሳ ሥጋ ብቻ ነው፤ ከዓሣና ከአንበጣ በስተቀር። የማይፈቅደው:- ሥጋ በሎች፥ የዓሳማዎች የውሻ ዝርያዎች፥ የአህዮች፥ የበቅሎዎች እና የሌሎችም ሥጋ ነው።

አንድ ክርስቲያን፥ ሙስሊም ጓደኛውን በሚጋብዝበት ጊዜ ሥጋውን ከሙስሊሞች ቄራ ቢገዛ እንኳን ጓደኛው በመጠራጠር ከክርስቲያኑ ጋር ለመብላት ላይደሰት ይችላል። መቀቀያው ድስት የዓሳማ ሥጋ ተቀቅሎበት ሊሆን ይችላል ብሎ ይሰጋል። ከሁሉ የከፋው ደግሞ ክርስቲያኖች ለሙስሊሞች በተዘጋጀው ምግብ ውስጥ የዓሳማ ጮማ በመጨመር እንደሚያታልሉ የሚሰማው ነው። ይህም ደግሞ ተደርጓል! ይሁንና የተደረገው በስመ-ክርስቲያኖች ነው። የተወሰኑ ክርስቲያኖች፥ ሙስሊሞች ከተለወጡ በኋላ ወደ ክርስቲያናዊ ኅብረት ለመቀላቀል የዓሳማ ሥጋ እንዲበሉ እንደጠየቁአቸው ለመረዳት ችለናል። ይህ ምን ዓይነት አስቀያሚና

እንዲበሉ እንደጠየቁአቸው ለመረዳት ችለናል። ይህ ምን ዓይነት አስቀያሚና የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት ያልተከተለ ነው!

ስለሆነም ሙስሊሞችን ስንጋብዛቸው ፈቃደኛነት ከእነርሱ ዘንድ ከታጣ ባናስገድዳቸው መልካም ነው። ባጠቃላይ አነጋገር አንድ ሙስሊም በራሱ ክልል የበለጠ ነፃነት እንደሚሰማው ከልምዳችን ለመረዳት ችለናል።

ቅዱሳት መጻሕፍት በበርካታ ሙስሊሞች ዘንድ ከፍተኛ ግምት ይሰጣቸዋል። ይህ በተለይ የሙሴን ሕግ፣ የዳዊትን መዝሙር፥ የኢየሱስን ወንጌልና ቁርዓንን ያጠቃልላል ወይስ መጽሐፍ ቅዱስንና ቁርዓንን ብንል ይሻላል።

በርግጥ ክርስቲያኖችም ለመጽሐፍ ቅዱስ ከፍተኛ አክብሮት አላቸው። አክብሮቱም ፍጹም የተለየ ነው። እኛ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ ምንባቦች ላይ ስናሠምርና ማጣቀሻችንን ከግርጌው ስንጽፍ፥ ወይም መጽሐፍ ቅዱሳችንን ጠረጴዛችን ላይ ስናስቀምጥ፥ ይህ በአንድ ሙስሊም እንደ ማርከስ ይቆጠራል። ቁርዓንን ለማንበብ እንኳ የሚከፍትባቸው ጊዜያት እጅግ የተወሰኑ ቢሆኑም ሁልጊዜም ከፍ ባለ መደርደሪያ ላይ አስቀምጦና ምናልባትም በተለየ ዓይነት መለበጃ ለብዶ ያኖረዋል። መጽሐፉን ከመንካቱ ወይም ከማንበቡም በፊት እጁን ይታጠባል። በባህል-ሙስሊምንና የቁርዓን ክፍሎችን እንደ ማህተብ ለመከላከያ ይጠቀሙበታል። ልዩነቱን ለማየት እንችላለን? በእስልምና እንደዚህ የሚከበረው መጽሐፉ ነው። እኛ የምናከብረው የመጽሐፉን ይዘት ማለትም መልዕክቱን ነው። እንደዚህ አድርገን ብናስቀምጥለት፥ አንድ ሙስሊም ይጽፋው ይሆናል ነገር ግን ሐቁ ይህ ነው አንድን አማካይ ሙስሊም ብንወስድ ቁርዓንን በራሱ ጥረት ለማጥናት አይሞክርም። በእስልምና ሃይማኖት ውስጥ የጋራ አመለካከቶች የቡድኖች ትምህርት እንጂ ግላዊ የጥናት ውጤቶች አይደሉም።

ጽዮናዊነት እና እስልምና ጠላቶች ናቸው። ዳሩ ግን በጥልቀት ሲታይ በሙስሊሞች የተጠላውከጽዮናዊነትም የላቀ ነው። ምናልባት ፀረ-አይሁዲነት ሊሆን ይችላል። (ዐረቦች ራሳቸው ሴማውያን ስለሆኑ፥ ፀረ-ሴማዊነት ነው ለማለት ያዳግታል)። በዘልማድ ክርስቲያኖች የአይሁድ ደጋፊዎች ነበሩ፤ መሆንም ነበረባቸው። ነገር ግን ለዐረቦችም (ሙስሊሞችም) የሚገዳቸው፥ የሚወዱአቸውና የሚረዱአቸው መሆን ነበረባቸው። ከእስራኤልና ከአይሁዶች ጎራ መሰለፉ እንዲያውም እንደ ጥቃት የሚቆጠር ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የጳለስጢናን የባለቤትነት ይዞታን በተመለከተ የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ ሐቁን እያወቅን ዐረቦችን መደገፍ አስቸጋሪ ይሆናል። በመቀበል ላይ ያሉትን መከራና ፍትሕ-አልበኝነትም እንጠላለን። እንደፖለቲካው ሁኔታ ሁሉ ክርስቲያኖችም

ስሕተት ነው ወይም አይደለም ሳይሉ፥ ለሁለቱም ወገኖች በመረዳት ርኅራኄ ሊኖራቸው ይገባል።

ወደ ሙስሊሞች መቅረቡ በወዳጅነት መንፈስ ቢሆን ከሁሉ የተሞላ ነው። እንዲሁም አንድ ጊዜ ከሙስሊሞች ጋር ለመወዳጀት የነበረብንን ፍርሃት ካስወገድን የሚኖሩን አጋጣሚዎች ብዙ ይሆናሉ። በአጠቃላይ ሙስሊሞችም እንደ ሌላው ሰው ሁሉ ያልተቆጠበ ተቀባይነትንና ፍቅርን የማግኘት ፍላጎት አላቸው። የጠለቀ የልብ ሸክም መካፈልም ሌላው ፍላጎት ነው።

ዳሩ ግን ቤተክርስቲያን በክልሏ ያሉትን (የሙስሊም) ቤቶች ሁሉ በመጎብኘት፥ በበለጠ ብልሃት ለመሥራት (በተስፋ) ልትወስን ትችላለች። ይህ እንግዲህ የቤት ለቤት አገልጎት መሆኑ ነው። እዚህ ላይ አቀራረቡ የተለመደ ባይሆንም፥ አገልጋዩ አስቀድሞ ራሱን በማስተዋወቅ የመምጣቱን ዓላማ መግለጽ አለበት። ምርጫው ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ በሚለው አቀራረብ ላይ ነው። «የዚህን አካባቢ ሃይማኖታዊ ጥናት እያካሄድን ስለሆነ፥ ለጥቂት ደቂቃዎች በመጠየቂያ ቅጽ ውስጥ እንድትሞሉልን በትሕትና እንጠይቃለን»። መጠይቁ በጥሩ ሁኔታ የተዘጋጀ እንደሆነ፥ ወደ ወሳኝ ጥያቄዎች ያመራል። ይህም በበኩሉ ወደ ፍሬያማ ምስክርነት ያደርሳል። ዳሩ ግን በመጀመሪያ ደረጃ ከአንድ የሙስሊም ቤተሰብ ጋር ወዳጅነት መመሥረት፥ ወይስ በቀጥታ ወደ ነጥቡ መምጣት እንዳለበት መስካሪው መወሰን አለበት። እኔ ደረጃ በደረጃ ወንጌል ማዳረሱን እመርጣለሁ። (የመጠይቁ ናሙና ከመጨረሻው ላይ ይገኛል)።

ምንም ልምምድ የሌላቸው ክርስቲያኖች ምናልባት ለሙስሊሞች ተለይቶ የተዘጋጀ ሥነ-ጽሑፍ፥ ወይም ተስማሚ ክርስቲያናዊ የቪድዮ ፊልም ይጋብዙ ይሆናል። አነስተኛ ልምምድ ያላቸው ሌሎች ምናልባት ለቤተሰቡ ዕለታዊ የጽሞና ጊዜን በማስተዋወቅ ይጎበኙዋቸው ይሆናል። በዚሁ ጊዜ ሙስሊሞቹ ወደ ዕለታዊ የጸሎት ጊዜያቸውን ሊጠቁሙዋቸው ይችላሉ። በርግጥ ይህን ታማኝነታቸውን ልናወድስላቸው ይገባል። ዳሩ ግን እኛ ይህንን ስንል የሳላት መከናወን ሳይሆን፥ ሁለት ክፍሎች ያሉትን ጽሞና እንደሆነ መግለጽ አለብን። ይኸውም የእግዚአብሔርን ቃል ማዳመጥና ባልተሸመደደ ግላዊ ጸሎት የያዘ መሆኑን ነው።

ይህን ጊዜ ሙስሊሞች አዘውትረው ባያደርጉትም እንኳ ቁርዓንን ስለማንበባቸው ሊናገሩ ይችላሉ። «በየቀኑ ቁርዓን ታነባለህ?»። ቢባሉ መልሳቸው « ... በየቀኑ እንኳ አይደለም» ሊሆን ይችላል። ይሄኔ መንፈሳዊ ውይይት ተጀመረ ማለት ነው።

የበለጠ ቀጥተኛ አቀራረብ ደግሞ:- «አሁን ብትሞት ምን እንደሚደርስብህ ታውቃለህን?» ወይም «በሞትሕና በእግዚአብሔር ፊት በቆምህ ጊዜ፥ በምን

መመዘኛዎች ወደ መንግሥቱ እንደሚያስገባህ ተስፋ ታደርጋለህ?» ብሎ በመጠየቅ ሊሆን ይችላል።

በእኛ በኩል የዚህ ዓይነቱ አቀራረብ በእርግጥ ለመንፈሳዊ ውይይት የበር መክፈቻ ብቻ ነው። ፍቅር ያላቸው ክርስቲያኖች ለወንጌል ማሠራጫ የሚሆኑ ሌሎች ብዙ መንገዶች ለማሰብ ይችላሉ።

ጥያቄዎችን በመጠየቅ ውይይቱን ለመጀመር በጣም ጥሩ መንገድ ነው። ከሁሉም በፊት ብዙ ሰዎች ስለ ራሳቸው ስለ ስሜታቸው፥ ስለ ሁኔታቸውና እምነታቸው እንዲናገሩ ሲጠየቁ ደስ ይላቸዋል። ማዳመጥ ደግሞ በጣም አስፈላጊ የውይይትገጽታነው። በ«መልእክታችን»፥ ወይም በ«ምስክርነታችን»፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እንኳ ቢሆን ሌላውን መደብደብ፥ እነርሱን ወደ ተቃዋሚነት መገፋፋት ወይም ወደማይፈለግ አለመግባባት መጋበዝ ነው። የሚጠየቁ ጥያቄዎች ለተጨማሪ መንፈሳዊ ውይይት የሚጋብዙ መሆን አለባቸው፡-

«በቀን አምስት ጊዜ እንደምትጸልይ ሰምቻለሁ (ተረድቻለሁ)። ለምንድነው እንደዚህ የምታደርገው? ለምንድነው ሁሉም ሰው እንዲህ የሚያደርገው? ጸሎቱን ለ 10000 ጊዜያት ከደጋገምህ በኋላ፥ እንዴት እውነተኛ አምልኮ ይሰማሃል? ከጥቂት ጊዜ በኋላ እንዲያው ልምድ ብቻ ሆኖ መቅረቱ አይደለምን?»

«መሥዋዕት እንደምታቀርብ ሰምቻለሁ (ተረድቻለሁ)። እግዚአብሔር ለአብርሃም ወይም ለሙሴ እንዳዘዘው ላለ ዓላማና ነው የሚደረገው? መሥዋዕት ማቅረብ ምን ውጤት አለው?

«ሙስሊሞች እስልምና የአብርሃም ሃይማኖት እንደሆነ ይመስላቸዋል። በምን መንገድ?»

«ወደ መካ (ሐጂ) በሚደረገው የተቀደሰ ጉዞ ላይ ተካፍለህ ታውቃለህ? በብዙ መቶዎችና ሺዎች ከሚቆጠሩ ሌሎች ሙስሊሞች ጋር በዚያ መሆን ምን ስሜት ያሳድርብሃል? ይህ ብዙ ገንዘብ አይጠይቅምን? በካዕባ ያለውን ጥቁር ድንጋይ የምትስመው ለምንድነው?

ጥያቄዎቹን የሚጠይቀው ሰው የመጽሐፍ ቅዱስ መልሶቻቸውን ማወቅ እንዳለበት መቼም ግልጽ ነው።

ህልቆ መሳፍርት የሌላቸው ጥያቄዎች አሉ። እያንዳንዱ ጥያቄ ሙስሊሙ ወዳጅህ ማሰብ እና ማወዳደር እንዲጀምር የሚያደርገው ሆኖ መታቀድ አለበት።

ሙስሊሞችን በወንጌል ለመለወጥ አስማትነት የለውም። ለቀቅ አድርጉን ሊሉንም ይችላሉ፤ ወይም ብዙ ጥያቄዎች ሊጠይቁን ይችላሉ፤ ብዙ ጊዜ

አጋጥሞናልና። በዚሁ ጊዜ:- «መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል ...» በማለት የእግዚአብሔርን ቃል ልናካፍላቸው እንችላለን።

ብልሃትና መረዳት እንዲሁም በጎ አስተያየቶች አስፈላጊነታቸው መቼም የታወቀ ነው። ወደ አንድ ቤት ስንገባ እንግዶች ነንና እንደ እንግዳ እንሁን! መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ፥ ወይም መንፈሳዊ ውይይት በመምራት ላይ እያለን ዘመድ ወይም ጓደኛ ለጉብኝት ቢመጣ፥ አስተናጋጁን ማሳፈር አይገባንም። ይልቁንም እርሱን ላለማሳፈር መጽሐፍ ቅዱሱን ገለል ማድረግና ለጊዜው የጨዋታውን ርዕስ መቀየር ያስፈልጋል። ሙስሊሞች ሌሎች ሙስሊሞችን ስለሚፈሩ እንደዚህ ሲተባበሩአቸው ደስ ይላቸዋል።

ውይይቱን መምራት ብዙውን ጊዜ በጣም አስፈላጊ ነው። ሙስሊሞች ለመመለስ ዐቀበት የሚሆንባቸውን ርዕስ የመዝለልና ራሳቸውን ለመከላከል ሲሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ጥቃት የመሰንዘር ጠባይ አላቸው። መልሱን ለማዳመጥ ሳይፈልጉና ከጉዳዩ ጋር አግባብ የሌላቸውን ጥያቄዎች ሲመርጡ፥ መስካሪው ውይይቱን ሥርዓት ባለው ሁኔታ መምራት አለበት። ይህ ካልሆነ ግን እርባና የሌለው የክርክር መድረክ ይሆናል።

ስሜታዊነት፡- ሙስሊሞች በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ወይም በኢየሱስ ላይ መሠረት የሌላቸው የተቃውሞ ቃላት ሲሰነዝሩ ስሜታዊነት ሊንጸባረቅ ይችላል፤ ይሄኔ ነው ዝግ ማለት። ከመገንፈል የሚገኝ ምንም ጥቅም የለም። እንዲሁም ክርክሩ ከቁጥጥር ውጭ ቢወጣ ምንም ትርፍ አይገኝም። እርግጥ አንዳንዱ የእስልምና ክርክሮች ትዕግሥታችንን ለማስጨረስ ታቅደው የሚቀርቡ ናቸው። ቢሆንም በሚገባ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር ሆነን እንደ ክርስቶስ መሆን ይገባል። ነጥባችንን በግልጽ ማብራራት ትልቅ ጠቀሜታ አለው። ሁሉም ስውር ቂቅ አሳብ በቀላሉ ሊገባው አይችልም። በተወሰኑ ባህሎች የቋንቋ አጠቃቀም እንኳ ምልክታዊ ወይም ሥዕላዊ ነው። የሁሉንም ረቂቅ አሳቦች የማስተላለፍ ሂደት መንፈሳዊውም አቀራረብ ሁሉ ይኸው ነው ምሳሌዎችን፥ ሥዕላዊ መግለጫዎችንና ተመሳሳይ ማብራሪያዎችን በማምጣት ማስረዳት ይቻላል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚሁ ዘዴ ማስተማሩ ልማድ አድርጎት ነበር። ይህም እንደዚያው እንድናደርግ ሊገፋፋን ይገባል። ዳሩ ግን መግለጫውን ከኑሮአችን ጋር አዛምደን መጠቀም አለብን (በመጨረሻ ጽሑፉ ላይ የተወሰኑ ምርጥ ምሳሌዎች ቀርበዋል።)

ክርስቶስን እንደተቀበሉ መወሰናቸውን ከሙስሊሞች እንኳ ቢሆን የሚጠበቅ ነው። ይህን በአንድ የምስክርነት ጊዜ ሳይሆን፥ በሂደት ሊከናወን ይገባል። ሙስሊሙ ወደዚህ ነጥብ የሚደርሰው ክርስቶስን ሲቀበል፥ ማለትም ለኃጢአቱ የሞተለት የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑና የእግዚአብሔር ስጦታ የሆነውን ምሕረትና በኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ላይ ሞት የተገኘውን አዲስ ሕይወት ሲያገኝ ነው። ምንም እንኳ ቅርፁ «ከልማዳዊ» ሁኔታዎች ሊለይ ቢችልም፥ የእምነት ይዘቱ ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ መመሥረት አለበት። ምናልባት አሁንም አንዳንድ ያልተመለሱ ጥያቄዎች ይኖሩ ይሆናል። እነዚህ መሠረታዊ ባሕርይ እስከሌላቸው ድረስ፥ በነዚህ ጉዳዮች መረበሽ የለብንም። ይልቁንም የእግዚአብሔር ቃል በጊዜው ምላሹን በግሉ እንዲሰጠው መጸለይ አለብን። መንፈስ ቅዱስም ይመራናል!

በአጠቃላዩ ደንብ መሠረት እስካሁን ድረስ ሙስሊሙን ወደ ቤተክርስቲያን ጉባኤ መጋበዝ የለብንም።

ሙስሊም «የመረማመጃ ደረጃዎችን» ይፈልጋል፡- ወደ ቤተክርስቲያን ለመምጣትናበዚያምየሚደረገውንለመረዳትለሙስሊሙመረማመጃዎች አስፈላጊዎች ናቸው። በመስጊድ ውስጥ የጁማን የጉባኤ አምልኮ ተካፍለህ ታውቃለህ? ምናልባትም ተካፍለህ አታውቅም ይሆናል። ተካፍለህ ከሆነም የመከፋት ስሜት ተሰምቶህና ብዙ ጥያቄዎች በአዕምሮህ ውስጥ ተመላልሰው ይሆናል። አንድ ጊዜ በቤተክርስትያን የስብከት አገልግሎት ስለነበረኝ፥ ወደቤታችን ሊጎበኘን ለመጣው ሙስሊም ወደ አገልግሎት እንደምሄድ ነገርሁት። ከእኔ ጋር ቢመጣ ቅር ይለኝ እንደሆን በጉጉት ጠየቀኝ። ቅር እንደማይለኝ ነገርሁትና መጣ። ዳሩ ግን ከመጨረሻው መቀመጫ ላይ መቀመጡን መረጠ። በኋላ እጅግ እንደተጨነቀና በማንኛውም ጊዜ ከቤተክርስቲያኑ ወጥቶ ለመሸሽ ፈልጎ እንደነበር ነግሮኛል።

ሰዎች ያሉባት «ቤት ቤተክርስቲያን» ዓይነተኛ «የመረማመጃ ደረጃ» ልትሆን ትችላለች። ከአንዳንድ በሳል ክርስቲያኖች የመጽሐፍ ቅዱስን መሠረታዊ ነገሮች ይገነዘባል። እንዴት እንደምንጸልይ፥ እንደምንዘምርና በአምልኮም ላይ የምናደርገውን ደረጃ በደረጃ እያየ ይማራል። ዳሩ ግን ይህች «ቤት ቤተክርስቲያን» የተለመደው የወንጌል ስብሰባ የሚካሄድባት ዓይነት መሆን የለባትም! ሙስሊሙ ለምንና ለማን እንደሚወስን ማወቅ አለበት!!

ከውሳኔ በኋላ ሥራው ተጠናቀቀ ማለት አይደለም። አዲሱ ዓማኝ የሚደግፉትን፥ የሚረዱትንና የሚመክሩትን ክርስቲያን ጓደኞች ይፈልጋል። በቤት ውስጥ ሊኖረው የሚገባው ሥነ-ምግባር እንዴት ያለ ነው? አዳኙን እንዳገኘ ለቤተሰቡ እንዴት መናገር

አለበት? ተቃውሞና ስደት ሲመጣበት እንዴት መቋቋም አለበት? አሁን የኅሳማ ሥጋ መብላት ይኖርበታልን? ስለ ደምስ? የልምድ ጸሎቶችስ? ጥያቄዎችና ችግሮች ሲመጡ አስተዋይና በሳል ምክር ሊሰጠው ያሻል።

ላልተወሰነ ጊዜ አዲሱ አማኝ ከክርስቶስ ጋር በጀመረው አዲስ ጉዞው ላይ አብሮት የሚጓዝ ባልንጀራ ያስፈልገዋል። በጸሎት መበርታትና ከቃሉም መማር አለበት። የቀድሞ ዓለም ስለሚቃወመውና የሚኖርበትን አዲስ ዓለም በማግኘቱ ረገድ እገዛ ያሻዋል። የዚህ ዓይነቱ ሰው ራሱን ወይም ራሷን የሰጠ/ች ደቀመዝሙር እስኪሆን/ትሆን ድረስ ችግሩን መረዳት፥ ቸርነትና ግላዊ እንክብካቤ ማድረጉ መቀጠል አለበት።

## ረ. ለሙስሊም ወንጌል የማድረስ ዘዴ

ሁለት ዓይነት የወንጌል ሥርጭት ዘዴዎች አሉ፦

ሀ) በጣም እስላማዊ ወይም የእስልምና መንግሥት ባለባቸውና በክርስትና እምነት ላይ ከፍተኛ ጥላቻ በሚያሳዩ አገሮች ወይም አካባቢዎች፥ እና

ለ) ሙስሊሞች በቁጥር አናሳ በሆኑባቸው አገሮች ወይም ሙስሊም አምባገነን ሳይሆን፥ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች በአንድ ክልል በሚኖሩባቸው አገሮች ማለትም የሃይማኖት ነፃነት በተረጋገጠባቸው ሥፍራዎች ናቸው።

ይህ የዘዴ በ «ለ» ሁኔታ ላሉት የተቀየሰ ነው።

ወንጌልን ለሙስሊሞች ለማድረስ የሚደረገው ጥረት ሁሉ ተቀባይነት እስካለው ድረስ፥ የሁሉም ወይም የብዙዎች ክርስቲያኖችና አብያተ ክርስቲያናት ወይም ቡድኖች የተባበረ ሥራ በጣም የተሻለ ነው።

**ዓላማው ሊሆን የሚገባው በተወሰነ ክልል ያሉትን ክርስቲያን ቡድኖች በጣም ለተዘጋጀ የወንጌል ስርጭት ማስተባበርና ማጠናከር ነው።**

### ማጠቃለያ

በጌታችን ኢየሱስ በተሰጠን ትእዛዝ ብርሃንና እንዲሁም በወቅቱ ካለው የእስልምና መነቃቃት አንጻር፥ ለሙስሊሞች ወንጌልን የማድረስ እንቅስቃሴ የክርስቶስ ቤተክርስቲያንና የአባሎችዋን ብርቱ ተሳትፎ የሚጠይቅ እንጂ ችላ ሊባል የሚችል አይደለም።

ይህ በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው! ለታላቁ ተልዕኮ ትእዛዝ ያለን እንድንገዛ፥ ለክርስቶስም ያለን ታዛዥነትና ስለሚጠፉትም ያለብን ኃላፊነት ችላ ማለት የለብንም። ትክክለኛውን ምርጫ እንድንመርጥም ተጠይቀናል። ይኸውም፦

> «አስቀድመን መከራ ተቀብለን ተንገላተንም፥ በብዙ ገድል የእግዚአብሔርን ወንጌል እንናገር ዘንድ በአምላካችን ደፈርን። ልመናችን ከስሕተት፥ ወይም ከርኩሰት፥ ወይም ከተንኮል አልነበረምና፥ ነገር ግን ወንጌልን አደራ ይሰጠን ዘንድ እግዚአብሔር የታመንን ሆነን እንዳገኘን መጠን፥ እንዲሁ እናንገራለን፤ ልባችንን የሚመረምር እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን ደስ እንደምናሰኝ አይደለም። እንደምታውቁት፥ እያቆላመጥን ከቶ አልተናገርንም

እግዚአብሔርም እንደምንመሰክር፥ እያመካኘን በመጎብኘት አልሠራንም፤ የክርስቶስ ሐዋርያት እንደመሆናችን፥ ልንከብድባችሁ ስንችል፥ ከእናንተ ቢሆን ወይም ከሌሎች ክብርን አልፈለግንም። ነገር ግን ሞግዚት የራሷን ልጆች እንደምትንከባከብ፥ በመካከላችሁ የዋሆች ሆንን፥ እንዲሁ እያፈቀርናችሁ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለማካፈል ብቻ ሳይሆን የገዛ ነፍሳችንን ደግሞ እናካፍላችሁ ዘንድ በጎ ፈቃዳችን ነበረ፤ ለእኛ የወደዳችሁ ሆናችሁ ነበርና። ወንድሞች ሆይ፥ ድካማችንና ጥረታችን ትዝ ይላችኋልና፤ ከእናንተ በአንዱ ስንኳ እንዳንከብድበት ሌሊትና ቀን እየሠራን፥ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለእናንተ ሰበክን። በእናንተ በምታምኑ ዘንድ እንዴት ባለ ቅድስናና ጽድቅ፥ ነቀፋም በሌለበት ኑሮ እንደሄድን፥ እናንተና እግዚአብሔር ምስክሮች ናችሁ» (1 ተሰሎንቄ 2፡2-10)።

**አመለካከቶቻችን ግንኙነቶቻችንን፥ እንዲሁም ለሙስሊም ወንጌልን በእውነት ለማካፈል ያለንንም የጥረት ውጤት በከፍተኛ ደረጃ ይወስናሉ። ይህ የሞትና የሕይወት ጉዳይ ነው።**

## ቅጥያ 1

## እ.ኤ.አ. ኅዳር 1989 - አቡጃ፥ ናይጀሪያ

እ. ኤ.አ.የኅዳር 1989 ጉባዔ የእስልምና በአፍሪካ ድርጅት መግለጫ (እስላማዊ ድርጅት ጉባኤ - ኦ.አይ.ሲ. እና አዲስ የተመሠረተው የእስልምና ድርጅት በአፍርካ - አይ.ኤይ.ኦ. የተባሉት በኅብረት የእስላማዊ ምክር ቤት፥ ለንደን በሚል ስም ሥር የተላለፈ መግለጫ)

በሚገባ ሥሩን የሰደደና ለእስልምና ጥቅሞችና እስከ አሁን ጸንተው ባሉት አስተሳሰቦች ላይ ቋሚ እስላማዊ አካል ለማዋቀር ተወስኗል። ይህም አካል በአፍሪካ የሙስሊሞችን ተስፋዎችና ፍላጎቶች እንዲገልጽ፥ በሙስሊም ማኅበረሰቦችና ድርጅቶች በተለያየ ገጽታ የተሠራውን የእስልምና ሥራ እንዲያስተባብር፥ በክፍለ ዓለሙ እና በጠቅላላው በሙስሊም ዓለም ያሉትን ሙስሊሞች ሕይወት ለማሻሻል የሚረዱ ፕሮጀክቶችን እንዲያቋቁም ሆኖ ተዋቅሯል። ለዚሁም እኛ ተወካዮች እዚህ አቡጃ ላይ በጁማዳ የመጀመሪያ ቀን አል አዋል፥ 1410 (28/11/89) ተሰባስበን የሚከተሉትን ለማድረግ እንወስናለን፡-

በአፍሪካ ላሉት ሙስሊሞች ሁሉ የኡማ (እስላማዊ ወንድማማችነት) አካላት በመሆን እንዲተባበሩ ጥሪያችንን ለማስተላለፍ፥ ይህም የአላህ መልእክተኛ (ፒቢዩኤች) መሐመድ ባመጣው ምሪትና ምሕረት የተባረከ ነው (ለአላህ ምስጋና ይሁን)።

የቅኝ ግዛትና የፀረ-እስልምና ፍላጎቶችን እንዲያሟሉ ሆነው በኤምፔሪያሊስቶች በተዘጋጁ የሰው-ሠራሽ ድንበሮች ጂኦ-ፖለቲካዊ ጋሬጣዎች ሳቢያ የተራራቁትን ሙስሊሞች በሙስሊሙ ዓለም ካሉ ወንድሞቻቸው ሁሉ ጋር የሁሉ ቻዩን የአላህን ትዕዛዛት እንዲያሟሉ ለማድረግ የተወሰነውን ጠንካራና የተባበረ ኡማን መልሶ በማቋቋሙ ረገድ እንዲተባበሩ ለመገፋፋት፥ እርስ በእርሳቸው እንዲተባበሩና በዚህም ዓላማዎች መካከል አንድነትን በመመሥረት ከጠቅላላው የሙስሊም፥ ኅብረተሰብ፥ በተለይም ከወጣቱ ጋር አንድነትን እንዲፈጥሩና ሁሉንም ዓይነት ጋሬጣ ከመካከላቸው ለማስወገድ እንዲጥሩ ጥሪ ለማስተላለፍ።

ሙስሊሞች በተለያዩ የትምህርት ተቋሞች ውስጥ የሚገኘውን የትምህርት መርሐ-ግብር (ካሪኩለም) እንዲገመግሙ እና ወደ እስልምና አስተሳሰቦች፥ ግቦችና መመሪያዎች እንዲሞከሩ ጥሪ ማስተላለፍ፥ እንዲሁም የኅብረተሰባቸውን ፍላጎት የሚያሟላ እንዲሆን ማድረግ ሲሆን ሙስሊሞች በሁሉም ደረጃዎች ለሴቶች ትምህርት ከፍተኛ ትኩረት እንዲያደርጉ ለመገፋፋት ነው።

በክፍለ አህጉሩ የጋራ ቋንቋ እና በተጨማሪም የቁርዓን ቋንቋ የሆነውን ዐረብኛ ፊደልን አጠቀቀም እንዲስፋፋ ጥረት ለማድረግ፥ የሙስሊም ወጣዎች በእስልምና አገልግሎት ውስጥ የሚያሳዩአቸውን ጥረቶች ጉባኤው በከፍተኛ አክብሮት የሚመለከታቸው ሲሆን፥ ለዚህ ጠቃሚ ጥረታቸውም ሙሉ ድጋፉን እንደሚሰጣቸው ቃል ይገባል።

በአፍሪካ እስላማዊ አገሮችና በሌሎች የሙስሊሙ ክፍላተ ዓለም መካከል ጠንካራ የኢኮኖሚ መተሳሰርን እንዲመሠርቱ ሙስሊሞችን ለመገፋፋት፥ ይኸውም በእስልምና መመሪያዎች ላይ የተመሠረተ አስተማማኝ የኢኮኖሚ መዋቅር ለመዘርጋት እንዲቻል፥ በንግድ፥ በኢንዱስትሪና በፋይናንስ የጋራ አገዛና ትብብር ለማቀለጣጠፍ ነው።

ጉባኤው በሸሪያ ሕግ የመተዳደር መብት የተነፈጋቸውን የክፍለ ዓለሙን ሙስሊሞች መሻት ይገነዘባል። እንዲሁም የሸሪያን ሕግ እንደገና ለማቋቋም በሚደረገው ትግል ጥረቶቻቸውን እንዲያጎለብቱ ይገፋፋል።

ጉባኤው የአፍሪካ ሙስሊም የመገናኛ ብዙሐን ማኅበር የማቋቋሙ ሄደት በናይጀሪያ በእንቅስቃሴ ላይ እንዲለ ይገነዘባል። ጉባኤው ይህን ዕፁብ እንቅስቃሴ በማድነቅ በመገናኛ ድርጅቶች ውስጥ ያሉ ሙስሊሞች ለስኬታማነቱ የሚፈልጋቸውን ሁሉ በማቅረብ እንዲደግፉት ይገፋፋል።

ከተወካዮቹ የበላይ ጠባቂነት ሥር እስላም በአፍሪካ ድርጅት በመባል የሚታወቅ አንድ ቋሚ አካል ለማቋቋም ከተካፋይ አገሮች ምርጫ ለማካሄድ፥ ከሌሎች ተግባሮች መካከል የመንግሥት እንቅስቃሴዎችን ለማዋቀርና የሚያስፈልጉት ግቦችና ዓላማዎች ከዚህ መግለጫ ጋር አባሪ ተደርጎ ተሰጥቷል።

ጉባኤው አክብሮቱንና አድናቆቱን በአንድነት:- ለጉባኤው ላሳዩት ትብብር ለናይጀሪያ ሕዝብ፥ መንግሥትና በተለይም ለናይጀሪያ ፕሬዝዳንት እና ለናይጀሪያ ጦር ጠቅላይ አዛዥ፥ ለጄኔራል ኢብራሂም ባባንግዳ አስደሳች የመክፈቻ ንግግር በመላካቸው ምስጋናውን ለማቅረብ ይፈልጋል። የመክፈቻ ንግግሩም ወደጉባኤው ተልእኮ ለንባብ የበቃው የናይጀሪያ ወታደራዊ ክፍል ኃላፊ በሆኑት በጄኔራል ሳኒ አባቻ ነበር።

* በለንደን የእስልምና ጉዳዮችና የእስልምና ምክር ቤት አስተባባሪ * ለሆነው ለናይጀሪያ ዋና ምክር ቤት፥

ጉባኤውን በማገዙና በማደራጀቱ ረገድ አስተዋጽኦ ላለው የእስልምና ጉባኤ ድርጅት (አ.አይ.ሲ)፥

* ለጉባኤው ስኬታማነት ላደረጉአቸው ጥረቶች ሁሉ፥ ለዕቅድ አውጪው ኮሚቴና ለሌሎችም ባለ ሥልጣኖች፥

* በጉባኤው ወቅት የጥናት ጽሑፎችን ላቀረቡና ስብሰባውን ለመሩ ሊቃውንትና ታዋቂ ሰዎች፥ እንዲሁም እግዚብሸኑን የበለጠ ውጤታማ በማድረግ የበኩላቸውን እገዛ ላደረጉት ሁሉ ምስጋናውን ያቀርባል።

የዓለም ሁሉ ፈጣሪና ጌታ በሆነው በአላህ አንድነት በመንፃት፥ «በእርግጥ በዚህ ዓመት (እስላማዊ) ኡማ አንድ ነው...» በሚለው ቁርዓናዊ እወጃ በመነቃቃትና በቁርዓን ውስጥ የሚገኘውን የአላህ መምሪያ «የአላህን ገመድ አጥብቀህ ያዝ፤ እንዲሁም መሐላዎቹን አታፍርስ» ለማሟላት በመወሰን፥ የእስልምና በአፍሪካ ጉባኤ ተሳታፊዎች በዚህ በመጀመሪያው ጁማዳ ቀን አል አወል፥ 1420 ኤ.ኤች.፥ (28/11/89) እስልምና በአፍሪካ ድርጅት (አይ.ኤ.አ) የተባለውን አካል ለመመሥረት ወስነዋል። ዓላማዎቹም የሚከተሉት ናቸው:-

* ከፍተኛ የሆነ የሰው ሀብት ዕድገት ፕሮግራም ለማካሄድ፥

* በአፍሪካና በሙስሊሙ ዓለም ለሚገኙ ሙስሊሞች በጠቅላላው አሳሳቢ ለሆኑ ጉዳዮች እንደ አፍ ሆኖ ለማገልገል፥
* ስለ እስልምና ታሪክ በአፍሪካ፥ ስለ ሙስሊሞችና ተቋሞቻቸው ከሐቀኛ እስላማዊ አመለካከታቸው አንፃር እንዲጽፉ ኤክስፐርቶችን ለመቅጠርና
* የዳዋህ ሠራተኞችን (ሙስሊም ሚሲዮናውያንን) ለማሠልጠን የተዋቀረ የእስልምና ኮሌጆችን፥ሠራተኞች እራሳቸውን እንዲችሉና አምራች እንዲሆኑ የሚያስችሏቸውን ሙያዎችንና ዕውቀቶችን ለማግኘት የሚሠለጥኑ፤ የሙያ ማሰልጠኛ ማዕከላት ለማቋቋም፥
* በዚህ ጉባኤ የተጀመረውን የወርቃማ ሥራ ቀጣይነት ለማረጋገጥ፥
* ለተዘረዘሩት ዓላማዎች ተግባራዊነት ከሌሎች ብሔራዊ ወይም ዓለም-አቀፋዊ እስላማዊ ድርጅቶች ጋር ለመተባበር፥
* በዓለም ሁሉ፥ በተለይም በአፍሪካ በሚገኙት ሙስሊሞች መካከል መንፈሳዊና ቁሳዊ አንድነት ለማሳደግ፥
* በአፍሪካ ሁሉ የዳ›ዋህን ሥራ ለማሳደግ፥ ለመደገፍ፥ ለማስተባበርና በመላው በክፍለ ዓለምም የእስልምናን ዕውቀት ለማሠራጨት፥
* በእስልምና ጉዳዮች ላይ የሚደረጉትን ምርምሮች ለማበረታታትና የምርምር ውጤቶቹንም ለማሳወቅ፥
* ወደተለያዩ የአፍሪካ ቋንቋዎች የእስላማዊ ጽሑፎችን ትርጉም ኅትመታቸውንና ሥርጭታቸውን ለማካሄድና ለማበረታታት፥
* ለሙስሊሞች ሁሉ የሼሪያን ሕግ መቋቋምና በሥራ ላይ መዋላቸውን ለመደገፍ፥
* የሙስሊም ወጣቶችን ከፍተኛ ተሳትፎ ለማጎልበትና የሴቶች መብቶችና ሚናዎች በማኅበረሰቡ ውስጥ ከሼሪያ ሕግ አንፃር እንዲጠብቅላቸው ከስምምነት ላይ መደረሱን ለማረጋገጥ፥
* በአባል አገሮች በተወሰኑ ብሔራዊና ዓለማቀፋዊ የስሥልጣን ወንበሮች ለሙስሊሞች ብቻ እንዲለዩ ማድረግ፥
* ከአባል አገሮች መካከል እስላማዊ ያልሆኑ ሃይማኖቶችን ሁሉ ከቅርፃቸውና ከሚያስከትሉአቸው ውጤቶች ጭምር ሙሉ ለሙሉ ለማጥፋት (እነዚህ ሃይማኖቶች፥ ክርስትና፥ አህማዲያንና እና በሙስሊሞች ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸውን ሌሎች የአምልኮ ዓይነቶችን የሚያጠቃልሉ ናቸው)።

* በአባል አገሮች ውስጥ በሁሉም ፖለቲካዊ የስሥልጣን ወንበሮች ሙስሊሞች ብቻ መመረጥ እንዳለባቸው ለማረጋገጥ፤
* ከአፍሪካ 24ኛ ከዓለም ደግሞ 46ኛ የ ብኦ.አይ.ሲ አባል የሆነችው ናይጀሪያ በተገቢው ጊዜ የእስላማዊ ፌዴራል ሱልጣኔት (ገዥ) መሆኗን ለማረጋገጥ። በመጋቢት 28/1990 እ.ኤ.አ. የሱኮቶ ሱልጣን የበላይ ሱልጣን ተብሎ ተሹሟል።
* የምዕራባውያንን የፍትሕና የፍርድ ዘዴዎች ሁሉ ከተከታዩ እስልምና በአፍሪካ ጉባኤ በፊት በአባል አገሮች ሁሉ በሸሪያ ሕግ መተካታቸውን ለማረጋገጥ፤
* በየጊዜው የስልምና በአፍሪካ ጉባኤን ለማደራጀት፤ በተጨማሪም ሴሚናሮችን፤ ሲምፖዚየሞችንና ወርክ ሾፖችን ለማዘጋጀት፤

ስለሆነም እነዚህን ጉዳዮች ከፍጻሜ ለማድረስ፤ ከሚከተሉት አገሮች ከተመረጡት አባላት፤ እንዲሁም ለንደን ከሚገኘው የስእልምና ምክር ቤት እና ከእስላማዊው ጉባኤ ድርጅት (ኦ.አይ.ሲ) መሪ ኮሚቴ ተቋቁሟል። አገሮቹም፡-

1. ናይጀሪያ 2. ኒጀር 3. ጋምቢያ
4. ሞሪታን 5. ሴኔጋል 6. ሊብያ
7. ታንዛኒያ 8. ሱዳን 9. ቱኒዚያ
ናቸው።

የእስልምና በአፍሪካ ድርጅት (አይ.ኤ.አ) የመሪዎች ዋና መሥሪያ ቤት አቡጃ፤ ናይጀሪያ ይሆናል። መሪ ኮሚቴው በናይጀሪያ መዋቅሮቹንና ሕጋጋቱን ጨምሮ በ6 ወራት ጊዜ ውስጥ እንዲያጠናቅቅ ግዴታዎች ተጥለውበታል። አይ.ኤ.አን እንዲያቋቁም የተለየ የሥራ መመሪያ ተሰጥቶታል። እንዲሁም ጉባኤው መሪ ኮሚቴው በእያንዳንዱ አባል አገር ውስጥ ብሔራዊ የፖለቲካ ፓርቲውን በብሔራዊ እስላማዊ ፓርቲ ለመለወጥ ዝርዝር ዕቅዶችን እንዲያወጣ ወስኗል። በመሆኑም የናይጀሪያ ብሔራዊ ሪፑብሊክ ማኅበር (ኤን. አር. ሲ) በናይጀሪያ ብቸኛ ዕውቅና ያለው እስላማዊ ፓርቲ በመሆን ይህን እቅድ ማገልገል አለበት። እነዚህ ተቀባይነት ያገኙት የፖለቲካ ፓርቲዎች ብቻ የመንግሥት (ውሳኔዎችን ማስተላለፍና ሕግ ማውጣት) የማስተዳደር ሚና ይጫወታሉ። ስለሆነም የናይጀሪያው ኤን.አር.ሲ እና ሌሎችም ፓርቲዎች የእስልምና ባሕርይ ያለውን ዓላማቸውን ለማንጸባረቅ ስማቸውን መለወጥ አለባቸው።

ጉባኤው በተጨማሪም ለጊዜው አይ.ኤ.አ. መቀመጥ ያለበት ለንደን በሚገኘው በእስልምና ምክር ቤት እንጂ ከኦ.አይ.ሲ መሆን እንደሌለበት ተስማምቶ ወስኖአል። (ይህም በናይጀሪያ አከራካሪ ሆኗል)።

የተባበረው ጉባኤ በመጨረሻም ኦ.አይ.ሲ. የእስልምና ጉባኤ ድርጅት ሙሉ አባልነት በመቀበል፥ ለ ኦ.አይ.ሲ. እስላማዊ ዕድገት 21 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር በልግስና በመርዳታቸው፥ የናይጀሪያን መንግሥትና ሕዝብ አመስግኗል።

እንዲሁም ለዓለሙ ሁሉ ናይጀሪያ እውነተኛ እስላማዊት አገር እንደሆነች ለማሳየት ሁሉንም የ ኦ.አይ.ሲ. ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ተግባር ላይ እንዲያውል የናይፌሪያን ፌዴራል መንግሥት አጥብቆ ጠይቋል።

እስላማዊ ምክር ቤት

ለንደን

# ቅጥያ 2

## በሙስሊም የወንጌል ሥርጭት ውስጥ መጠቀም የሚያስፈልጋቸው አገላለጾች

**የንጉሡ አዳዲስ ልብሶች - ሰው ሁሉ የሚያምነውንና የሚያደርገውን ማድረግ የግድ ለእውነት መስጠት አይሆንም።**

ለአለባበሱ ጥንቃቄ ለማድረግ ወደሚወደው ንጉሥ ዘንድ አንድ ነጋዴ መጣ። ይህ ሰው የንግድ ሰው ብቻ ሳይሆን አጭበርባሪ ቢጤም ነበር። ዕቃዎቹን ሁሉ ዘርግቶ ካሳየው በኋላ ወደ ንጉሡ ቀረብ በማለት በከፍተኛ የመተማመን ስሜት:- «አሁን እጅግ ዘመናዊውን ላሳይዎት ይገባኛል። ይህም ከልብሶች ሁሉ በላይ የተዋበ ነው። በጣም የተለየ ገፅታ ያለውን ማየት የሚችሉት ብልህ ሰዎች ብቻ ናቸው፤ ሞኞች ለማየት አይችሉም!» ይለዋል። በዚያውም የዕቃ መያዣውን በመፍታት ሰውሩን ነገር ለንጉሡ «አሳየው»። ንጉሡም ሞኝ ተብሎ ላለመሰደብ በመጠንቀቅ ጨርቁን አደነቀው። ባለጨርቁም ከዚያ የተሠራውን ልብስ እንዲጎናጸፍ ገፋፋው። ከሳምንት በኋላ ንጉሡ አዲሱን ልብስ በመጎናጸፍ በዋና ዋና ጎዳናዎች ላይ እንደሚዞር በግልጽ ታወጀ።

በርካታ ሕዝብ በጎዳናው ላይ በመሰለፍ ንጉሡን «የልደት ልብሱን» ተጎናጽፎ አየው-ራቁቱን። ዳሩ ግን ሽጋውን ልብስ «እህ ... እህ ...» እያሉና እጃቸውን እያጨበጨቡ አደነቁለት። ንጉሡም ጨምሮ ማንም ሰው ሞኝ ሊባል አልፈለገም። አንድ ትንሽ ልጅ ብቻ ወደ ንጉሡ እያመለከተ «ራቁቱን ሰው እዩት!» በማለት ጮኸ።

«ስውሩ ዕቃ» ለእኛ «የተሸጠልን» ሃይማኖት ሊሆን ይችላል። ማንም ሰው ደግሞ ሞኝ ለመባል ስሕተት ሊሆን የሚችለውን ነገር እንበኢ ለማለት አንደፍርም። ሁሉም ሰው ከኅብረተሰቡ ለመገለል ስለሚፈራ ጥያቄዎችን ለማንሣት ወይም ተአማኝነቱን ለመጠራጠር አይፈልግም።

**ደኅንነትን ለማግኘት ቁልፍ የሆነው እምነት ያስፈልጋል**

ከግዴለሽ፥ ካለማስተዋልና ከቸልተኛ ባሕርያቸው የተነሣ የተወሰኑ ሰዎች በአምባገነኑ መንግሥት ተወስደው በማረፊያ ቤት ታጎሩ። እነርሱም ለጊዜው በሥፍራው ያልነበረው ንጉሥ ሲመለስ የሞት ቅጣት እንደሚፈረድባቸው ታውቆ

ነበር። አንድ ጥሩ ወዳጃቸው በዕጣ ፈንታቸው እንዳይጠፉ በመፈለጉ ነፃ ሊያወጣቸው ወሰነ። ወኅኒው ጠንካራ ስለነበረ ማምለጥ የማይሞከር ነበር። የወኅኒውን ጠባቂ በማሸነፍ ከአሰረው በኋላ ብቸኛውን ቁልፍ ቀማው። ቁልፉ ግን አገልግሎት ሊሰጥ የሚችለው ከውስጥ በኩል ብቻ ነበር። ስለዚህ መልካሙ ወዳጃቸው በሩን በመክፈት ወደ ቤታቸው እንዲመለሱ ለእስረኞቹ አቀበላቸው። እስረኞቹም ቁልፉን በማየት ስለጠቀሚታው ተወያዩ። መልካሙ ጓደኛቸው የበሩ ቁልፍ እንደሆነና እንዴትም እንደሚሠራ ነገራቸው። ጊዜ እንዳያባክኑም አስቸኮላቸው። ነገር ግን እስረኞቹ በተጨማሪ በመከራከር ይህች ትንሽዬ ቁልፍ ይህን ትልቅ በር ስለመክፈቷ ተጠራጠሩ።

አንዳንዶችም ቁልፉን እንዲያሳድጓት ወይም በወኅኒው እስካሉበት ጊዜ ድረስ ለመዝናኛነት እንዲጠቀሙባት አሳብ አቀረቡ። ሌሎች ደግሞ ቁልፍ የሚባልነገር እንደሌለና ይህንንም መፈለግ እንደማይገባ በመናገር ደመደሙ። በዚህም ጊዜአቸውን አባከኑ፤ ገዢውም መጣና ተገደሉ።

ዳኛውና ጓደኛው - የፍርድና ምሕረት መገናኛ ሥፍራ

ሰውየው ከመሥሪያ ቤቱ ጠቀም ያለ ገንዘብ በመስረቁ ወደ ፍርድ ቤት ቀረበ። ዳኛው ጉዳዩን እየሰማ ሳለ በሌብነት ተከስሶ የቀረበው እጅግ ከሚያቀርባቸው ጓደኞቹ መካከል አንደኛው እንደሆነ ተረዳ። ይህም የዳኛውን ልብ ለሁለት ከፈለው። የተከሳሹ ጓደኛው መሆን በጓደኝነትና እስራት መካከል የሥራ ኃላፊነቱ መካከል አዋዠቀው። ወደሚገባው ወኅኒ ሊያገባው ነውን?

በፍትሐዊ ዳኝነት በነፃ እንዲወጣ ለማድረግ አይችልም። እንዲህማ ከሆነ ለማስከበር የቆመለትን ሕግ ራሱ ይቃረናል ማለት ነው።

ዳኛው ሰውየው ለሕጉ ታማኝ በመሆን የወሰደውን ዕጥፍ አድርጎ እንዲመልስ ወይም ለ12 ዓመታት ወኅኒ እንዲወርድ ፈረደበት። ጓደኛውም በዚህ እጅግ ተጎዳ። እንኳንስ እጥፉን ይቅርና ከተሰረቀው ገንዘብ ጥቂቱን እንኳ ለመክፈል አይችልም ነበር።

በኋላም ትንሿ ክፍል የእስረኛው ተከፈተች ዳኛውም ገባ። ዳኛው የመጣው የችሎት ልብሱን ለብሶ ሳይሆን፥ ተራ ልብሱን ለብሶ ነበር። እስረኛ ጓደኛውንም ሕግ በመተላለፉ በመገሠጽ፥ የዳኝነቱን ትክክለኛነት አረጋገጠለት። ከዚያ በኋላ ግን እጁን ወደ ኪሱ በመስደድ አንዲት የወረቀት ቁራጭ አወጣና ለጓደኛው ሰጠው። ወረቀቱም ፍርዱ እንዲከፈል የጠየቀው ገንዘብ የተከፈለበት ደረሰኝ ነበር። ዳኛው ትንሽ

የተጠራቀመ ገንዘብ ነበረውና ጓደኛው በመከራ ውስጥ መሆኑን ሲያይ ለችሎቱ ከፈለለት። ቅጣቱ በመከፈሉ እስረኛው ተፈትቶ በዳኛ ጓደኛው ወደ ቤቱ ተወሰደ።

ልክ ከዛሬ 2000 ዓመታት በፊት ለእኛ የሚገባውን ቅጣት እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል እንደተቀበለው፥ ጽድቅና ጸጋ እዚህ ላይ ተገናኙ። እኛን በሲዖል ለዘላለም ከመሰቃየት ለማዳን የሞትን ቅጣት ስለ እኛ ተቀበለ።

«እና - ኩትሺ» - እና የእግዚአብሔር ልጅ

ማንም እውነተኛ ክርስቲያን ወይም ሙስሊም ኢየሱስ የተወለደው በእግዚአብሔርና በማርያም መካከል በተፈጸመው የግብረ-ሥጋ ግንኙነት አማካይነት ነው የሚለውን የድፍረት አሳብ አይቀበልም። ይህ በሁለቱም ክፍሎች የተጠላ አስተሳሰብ ነው። ምናልባት አንድ ሙስሊም «የእግዚአብሔር ልጅ» የሚለውን ሐረግ በሚሰማበት ጊዜ ወደ አዕምሮው ሊመጣ የሚችለውን የተሳሳተ አመለካከት ለመቅረፍ ገለጻ ያስፈልግ ይሆናል። በማለይ ቋንቋ መቆለፊያው «ኩትሺ» ሲባል፥ ቁልፉ ደግሞ «እናኩትሺ» ተብሎ ይጠራል። ይህም ቃል በቃል ሲወሰድ «የመቆለፊያ ልጅ ማለት ነው። ማንም ግላይ አንድ «ኩትሺ» ከሌላው «ኩትሺ» ጋር ግንኙነት አድርጎ «እናኩትሺ» እንደወለደ አያምንም። የቃሉ ግልጽ ትርጉም ቁልፉ ከመቆለፊያው ጋር ግንኙነት እንዳለውና ያለቁልፉም መቆለፊያው ሊከፈት እንደማይችል ለማብራራት ነው። ሁለቱም የማይነጣጠሉና አብረው የሚሠሩ ናቸው። መቆለፊያው ያለቁልፉ ጎደሎ ነው - እንዲያውም ዋጋ የለውም። በተመሳሳይ ሁኔታ በዐረቢያ፥ መንገደኛ «የመንገድ ልጅ» ይባላል። ይህም በኅብረተሰቡ ዘንድ የሚታወቅ የክልል መጠሪያ ነው። ስለሆነም ስለ ኢየሱስ ልጅነት ክርስቲያኖች ያላቸው ግንዛቤ ከዚሁ አኳያ ነው። እርሱ ወደ እግዚአብሔር ዘንድ የሚያደርሰንን መንገድ የሚከፍት «ቁልፍ» ነው።

ሥላሴ የሆነው እግዚአብሔር በመለኮታዊነቱ በሰብዓዊ አዕምሮ ለመረዳት አይቻልም፤ እርሱ ግን ራሱን ገልጿል።

የእግዚአብሔር የሥላሴ ፅንሰ-ሐሳብ በተገለጹት እውነቶች ላይ የተመሠረተ ሲሆን ከሰው አዕምሮ ያለፈ ነው። ስለሆነም ለመረዳት የሚያስቸግረውን ነገር በግልጽ ለማስቀመጥ እንችላለን እንዳንል ልንጠነቀቅ ይገባል።

ይሁንና ምሳሌ መጠቀሙ ምናልባት መረዳታችንን ትንሽ ያሳድገው ይሆናል። ለአንድ የኬሚካል ተመራማሪ (ኬሚስት) ለምርምር እንዲሆነው አንድ የውኃ ጠብታ ውሰድለት። እርሱም ይህ ውሃ ሁለት እጅ የሃይድሮፍን ንጥረ-ነገርና አንድ እጅ

አክስጂን እንዳለበት ይነግርሃል። ይህንኑ የውሃ ጠብታ ወደ ፊዚካል ተመራማሪ (ፊዚስት) ብትወስድለት ፈሳሽ መሆኑን ይነግርሃል።

አሁንም ጥቂት በረዶ ውሰድና እንዲሁ አድርግ። ኬሚስቱ የሃይድሮጅንና የአክስጅን ውሕደት ነው በሚለው ንግግሩ ሲጸና ፊዚስቱ ጠጣር ነው ይለዋል። አሁን ደግሞ የውኃ ትነት የሞላበትን የሙከራ ቱቦ (ቴስት ትዩብ) ውሰድ። ኬሚስቱ በመጀመሪያ የሰጠውን መልስ ይሰጥሃል፤ ነገር ግን የፊዚስቱ ምላሽ የተለየ ይሆናል። ተን ነው ይልሃል።

በእነዚህ ነገሮችና በሥላሴ ፅንሰ-ሐሳብ መካከል ያሉት ተመሳሳይነቶች አስገራሚ ናቸው። ውኃ፥በረዶ፥ ወይም የውሃ ትነት ከቅርጽ ልዩነታቸው ባሻገር፥ የሁለት እጅ ሃይድሮጅንና የአንድ እጅ አክስጅን ውሕደት እንደሆኑ፥ እንዲሁም እግዚአብሔርም በተለያዩ «መግለጫዎቹ» ሁልጊዜም እግዚአብሔር ነው።

ምናልባትም የሕይወት ሁሉ መሠረት የሆነውን ውኃን ፈጣሪ በሆነው በእግዚአብሔር አብ፥ በእጅ የሚያዘውን - በረዶውን አዳኝ በሆነው በእግዚአብሔር ልጅ፥ ተኑን ደግሞ በማይታየው፥ እግዚአብሔርን በሚገልጸውና በጽድቅ ይኖሩ ዘንድ ኃይል ሰጭ በሆነው - በመንፈስ ቅዱስ ብንመስላቸው ነገሩ ግልጽ ሊሆንልን ይችል ይሆናል። ይሁን እንጂ እነዚህ ሦስቱ አካላት አንድ እግዚአብሔርን የሚገልጹ ናቸው።

ሌሎችም ማመሳሰያዎች አሉ። ሰው ሥጋ፥ ነፍስና መንፈስ አለው። የፀሐይ ጨረርም ብርሃንና ሙቀት አለው። እሳት፥ ብርሃንና ሙቀት ሦስት ቢሆኑም በሌላ ጎን ስንመለከት አንድ ናቸው።

እንደዚሁም አዕምሮ፥ አሳብና ንግግር አንድ ቢሆኑም አንዱ ከሌላው የሚለይበት የራሱ የሆነ ባሕርይ አለው።

የካከስያኑ ልዑል ሳሙኤል የእግዚአብሔርን ጽድቅና ፍቅር ሲያብራራ

ሳሙኤል ከ200 ዓመታት በፊት የነበረ የካከስያን ሕዝብ ልዑል ነበር። ሕዝቦቹ ጎረቤታቸው ከሆነችው ከቱርክ ጋር በማያቋርጥ ጦርነት ውስጥ ነበሩ። አንድ ጊዜ በወታደሮቹ የቱርክን ከተማ ከበባት። እንደተለመደው እናቱም አብራው ነበረች። በአንድ ምሽት ድንገተኛ የሆነ ጥቃት ለመፈጸም ቢያቅድም ጠላቶቹ ነቅተው ይጠብቁት ነበር። ምስጢራዊ ዕቅዶቹ መና ቀሩና ድሉ ታጣ። ሳሙኤልም በቁጣ ገንፍሎ ወሬ አቀባዩ ከተገኘ በመቶ የጅራፍ ግርፋት እንደሚቀጣ አስታወቀ። አሁንም በትልቅ ምስጢር ሌላ ድንገተኛ ጥቃት ታቀደ፤ ውጤቱ ግን እንደ መጀመሪያው ነበር። በዚህ ጊዜ ግን ወሬ አመላላሹ ተያዘ - የሳሙኤል እናት ነበረች።

እናቱን ከቅጣቱ ቢያተርፍ ሁሉም ሰው ፍትሕ-አልባ እንደሆነ ይናገራሉ። እንዲሁም ደግሞ እናቱን ቢቀጣ፥ «ሳሙኤል ለእናቱ እንኳ ርኅራኄ የለውም»

ማለታቸው የተረጋገጠ ነው። በመጨረሻም ለሦስት ቀናት ከተደበቀበት ድንኳን ሲወጣ ወታደሮቹ ሁሉ በጉጉት ከበቡት። ኮስተር ባለ ሁኔታ ለሕዝቡ እንዲህ አለ «በወሬ ቅብብሎሽ ምክንያት ሁለት ድሎች ከማጣታችን በላይ ሰዎቻችንም ተገድለውብናል። ጥፋቱ ስለተፈጸመ፣ በሕጉ መሠረት የመቶ ጅራፍ ቅጣት መከናወን አለበት! ጽድቅና ፍርድ መጠበቅ አለበት» አለ።

እናቱም ፊቷ ገርጥቶ በፍርሃት እየተንቀጠቀጠች ወደ መግረፊያው ቦታ ተወሰደች። ገራፊውም ጅራፉን አነሣ። ነገር ግን የመጀመሪያው ግርፋት ከማረፉ በፊት ሳሙኤል እንዲህ ሲል ጮኸ:- «ቆየኝ - እርሷ እናቴ ነች። እኔም ከሥጋዋና ከደምዋ የወጣሁ ነኝ። ቅጣቱን ስለ እርስዋ እቀበላለሁ!» ልብሱን አውልቆ ወደ መግረፊያው ቦታ በመግባት «ገራፊ፣ ከወንጀለኛ ባነሰ ሁኔታ እንዳትሰነዝር ተጠንቀቅ። ኃላፊነትህን ተወጣ። በል ቀጥል»። ራሱን ስቶ እስኪወድቅ ድረስ ግርፋቱ ተረባረበበት። ... ዳሩ ግን ባስገራሚ ሁኔታ ሕይወቱ ሊተርፍ በቅቷል። ምናልባት ይህ ክስተት በታሪክ ውስጥ ከተመዘገቡት ሁሉ በላይ ከሆነው ከክርስቶስ ሁኔታ ጋር ሊመሳሰል ይችላል። እርሱ በሰብዓዊ አካል ውስጥ የተቀመጠ እግዚአብሔር ነበር። የጽድቅ ፍርድም መፍረድ ነበረበት፤ አለበትም። ነገር ግን በፍጹም ፍቅሩ የእኛን - የእኔን - ያንተን ኃጢአት በራሱ ላይ በማድረግ የዚህ ውጤት የሆነውን አስጨናቂ የመስቀል መከራ ተቀበለ። የከፋውን ሥጋዊ መከራ መታገሡ ብቻ ሣይሆን፣ ንጹሕና ቅዱስ የሆነው እግዚአብሔር በክርስቶስ ውስጥ በመሆን አስቀያሚና አሳፋሪ የሆነውን ኃጢአታችንን በራሱ ላይ አደረገ።

### የበሰበሱ እንቁላሎች - «በእውነቱ እንደዚያ የከፋን አይደለንም»

የሰውን አዕምሮ ቀስፎ የያዘው ትልቁ ሐሰተኛ ትምህርት በሁለንተናው ቅዱስ «ከሆነው እግዚአብሔር ጋር ራሱን ብቁ አድርጎ ለመኖር እንደሚችል የሚሰማው አሳብ ነው።

አምስት የበሰበሱ እንቁላሎችና አንድ ደሕና እንቁላል ቀላቅለን ከመታን በኋላ፣ የሁለቱን ውሕደት ለመብል ብናቀርብ ተቀባይነት ያገኛል ብለን መገመት አንችልም። በኃጢአትና በስሕተት የተበላሸውን ሕይወታችንንም እንደዚሁ ለቅዱሱ እግዚአብሔር አቅርበን፣ በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖራቸው ለመጠባበቅ አንችልም።

## ደግ ሥራዎች ኃጢአታችንን ለመሸፈን ይበቃሉን?

መኪና በመስረቁ ምክንያት ከዳኛው ፊት ስለ ቆመው ሰው አስብ። ይህ ሰው ከዚህ ቀደም ምን ያህል መልካም ሥራዎችን እንደሠራ መተረክ ቢጀምርና ከእነዚህም ሥራዎች የተነሣ ይቅርታ ተደርጎለት በነፃ እንዲለቀቅ ቢጠይቅ፥ ዳኛው ምን ብሎ የሚመልስለት ይመስልሃል? ዳኛው፡- «የአደረግሃቸውን መልካም ተግባሮች ብናደንቅም፥ እዚህ ላይ ስለ ጥፋትህ - ስለፈጸምኸው ከፉ ሥራ እንነጋገራለን። በዚያውም አንፃር ደግሞ እንቀጣሃለን» ብሎ መመለሱ የማይቀር ነው።

እንደዚሁም፥ በፍርድ ቀን በእግዚአብሔር ፊት በምንቆምበት ጊዜ፥ ኃጢአታችን ስለሚመለከት፥ እግዚአብሔር ባዘጋጀው መንገድ ኃጢአታቸው ላልተሰረየላቸው ሰዎች ዘላለማዊ ቅጣት የማይቀር ነው!

## ታላቁ ዋና - ራሳችንን እንዴት ማዳን (ወይም አለማዳን) እንደምንችል

የእግዚአብሔር ጽድቅና ቅድስና ከእኛ ተፈጥሮና የሕይወት እርምጃ ጋር ሲነፃፀር፥ እጅግ የተራራቀ በመሆኑ መሸጋገሪያ ድልድይ ልናበጅለት አንችልም። ማንንም ወደ መንግሥቱ እንዳይገባ ይከለክላል። ምክንያቱም መመዘኛው ጽድቅና ቅድስና ስለሆኑ ነው። ወደ መንግሥቱ ለመድረስ እግዚአብሔር ለእኛ ባደረገው ነገር ላይ ሙሉ ለሙሉ እንደገፋለን። በእውነቱ ብዙ ሙስሊሞች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመድረስ የሚያስፈልገውን ሁሉ ለማሟላት በራሳቸው አስተሳሰቦችና ጥረቶች በጣም እየሞከሩ ናቸው።

እኛ ሁላችን ከምሥራቅ አፍሪካ ዳርቻ ተነሥተን (ይህ ሥፍራ ዓለማችን ናት እንበል) ወደ ሕንድ በዋና ለመድረስ ብንሞክር (ይህ ሥፍራ መንግሥተ-ሰማያት ነው እንበል)፥ ይህን ያህል ርቀር ማን ሊደርስ ይችላል? አንዳንዶች ልክ ከባሕሩ እንደጠለቁ ወዲያው ይሰምጣሉ። ሌሎች ደግሞ በማዕበሉ ውስጥ በመዋኘት ይሰምጣሉ። አንዳንዶች ምናልባት 10፥20፥ ወይም 30 ኪሎ ሜትር ይጓዙ ይሆናል። ይሁንና ማንም እስከ ሕንድ ድረስ ለመዋኘት አይችልም?

እርሱን ለመሰለና እርሱ ባለበት ለመገኘት ብቁ ለመሆን የሚያስፈልገውን ሁሉ ለማሟላት እንደምንችል መገመት እግዚአብሔርን መሳደብ ማለት ነው። ከኃጢአት ሁሉ በማንጻት እርሱ ብቁ ካላደረገን በስተቀር፥ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት ተስፋ ልናደርግ አንችልም። እርሱም በክርስቶስ በኩል ይህንን አድርጎልናል። እግዚአብሔር የሚሰጠን ብቻ እንቀበላለን እንጂ ሙስሊሞች እንደሚያደርጉት፥ እንዴት ከሲዖል ሊያድነን እንደሚገባ ትዕዛዝ አንሰጠውም።

መሥዋዕት የእግዚአብሔርን ፍርድ፥ ኩነኔና ይቅርታን ይገልጻል

በዔደን የአትክልት ሥፍራ አዳምና ሔዋን ኃጢአት ከሠሩበት ጊዜ ጀምሮ፥ የእንስሳት መሥዋዕቶች እንዲያቀርቡ በእግዚአብሔር ታዝዘዋል። እነዚህም ለኃጢአተኞች ሁሉ ራሱን ብቸኛና ዋጋ ያለው ታላቅ መሥዋዕት አድርጎ ለመስጠት ወደሚመጣው እንዲያመለክቱ ተፈልገው የተዘጋጁ ናቸው። መሥዋዕት የሚያሟላውን ሁሉ ክርስቶስ ስለፈጸመ፥ በኃጢአተኞች ምትክ ከሞተ በኋላ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም።

ለዚህ ነው እንግዲህ መጥምቁ ዮሐንስ መጀመሪያ ኢየሱስን ባየ ጊዜ፥ «እነሆ፥ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» (ዮሐንስ 1፡29) በማለት የጮኸው። ክርስቶስ መሥዋዕት እንደሚሆን ከብሉይ ኪዳን የነቢያት ትንቢቶች ተረድቶ ነበር። ኢሳይያስ ከረዥም ጊዜ በፊት ስለ ክርስቶስ ተንብዮ ነበር፡- «እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤ ከእኛም እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ፤ እግዚአብሔርም የሁላችንንም በደል በእርሱ ላይ አኖረ። ለመታረድ እንደሚነዳ በግ በማስጨነቅና በፍርድ ተወሰደ፤ ስለ ሕዝቤ ኃጢአት ተመትቶ ከሕያዋን ምድር እንደተወገደ ከትውልዱ ማን አስተዋለ? ... እግዚአብሔርም በደዌ ያደቅቀው ዘንድ ፈቀደ፤ ነፍሱን ስለ ኃጢአት መሥዋዕት ካደረገ በኋላ ... ኃጢአታቸን ይሸከማል ... ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶአልና ... የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ተሸከመ» (ኢሳይያስ 53፡6-12)።

ይህ ከአዲስ ኪዳንም ድጋፍ አግኝቷል። «ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና» (1 ጴጥሮስ 3፡18)።

ንስሐ በራሱ በክርስቶስ ተገልጧል።

የጠፋው ልጅ ምሳሌ (ሉቃስ 15፡11-32)፡- ልጁ በርካታ በደል ቢፈጽምም ቅሉ፥ አባትዬው ልጁን እንደገና መቀበሉን የእግዚአብሔርን አፍቃሪ አባትነት የሚገልጽ ነው። ይህ ታሪክ በተለይ ለሙስሊሞች ጠቃሚ ነው። ደግሞም እግዚአብሔርን እንደባሪያ ወይም አገልጋይ በማገልገልና (ሙስሊም ለማድረግ እንደሚፈልገው) እንደ ልጅ በማምለክ መካከል ያለውን ልዩነት ስለሚያሳይ አስፈላጊ ነው። ምሳሌው እግዚአብሔር እርሱን እንደባሪያዎች እንድናመልከው ሳይሆን፥ የልጅነት ማዕረግ እንዲኖረን እንደሚፈልግ ያመለክታል። ምሳሌው ፍጻሜ የለውም። ታላቁ ልጅ የአባቱን ግብዣ ስለ መቀበሉ አልተናገረም። ስለሆነም እግዚአብሔር እያንዳንዳችን እርሱን እንደ አባት አውቀንና ልጆቹ ሆነን ለመኖር ግብዣውን

ለመቀበል ወይም ላለመቀበል ሙሉ ነፃነት ይሰጠናል። ይህ እንግዲህ የይቅርታ ጸሎታችንን ልንመሠርትበት የምንችልበት አመለካከት ነው። በጠፋው ልጅ ምሳሌ ውስጥ ኢየሱስ ሁለት ልጆች ስለነበሩት ሰው ይናገራል። አንደኛው የውርስ ድርሻውን ተቀብሎ እሩቅ አገር በመሄድ አባክኖ ጨረሰው። የዓሳማዎች እረኛ በመሆን ሲሠራ «ወደ ልቡ ተመለሰ»። በትኩረትና በታማኝነት ያለበትን ሁኔታ ገመገመ። አንድም ሐሳብ መጣለት። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን «ንስሐ» በማለት ተርጉሞታል። እንደዚህ ባለ ሁኔታ ቀጠለ:- ወጣቱ ውሳኔ አስተላለፈ፤ «(ሀ) ተነሥቼ (ለ) ወደ አባቴ እሄዳለሁና:- «አባቴ ሆይ፥ በሰማይና በፊትህ በደልሁህ፤ ወደፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም፤ ከሞያተኞችህ እንደ አንዱ አድርገኝ» (ሐ) እለዋለሁ። የተመኘው ነገር ቢኖር ወደ ጉስቁልና ከመራው ከዓሳማ እረኛነት ይልቅ የአባቱ አገልጋይ መሆንን ነበረ። ይህ ውሳኔ በጣም ጥሩ ነው (ምናልባት ከዚህ ቀደም እንዲህ ያሉ ውሳኔዎችን አድርገን ይሆናል)። ይሁንና ይህ በቂ አልነበረም። በምሳሌው ውስጥ የምንመለከተው ወጣት ውሳኔው ከመፈጸም አልቦዘነም:- «(መ) ተነሥቶም (ሠ) ወደ አባቱ መጣ»።

እጅግ የሚያስገርመው አባቱ ልጁን በመጠባበቅ ውጭ ውጭ እየተመለከተ ነበር። የበለጠ የሚያስደንቀው አባቱ ልጁን አወቀው። ቀደም ብሎ በልበ-ሙሉነት ቢፈረጥጥም፥ የተሳካ፥ ደስተኛና የተሟላ ሕይወት የመኖር ምኞቱ መክኖ ቀረ። እንደ ቆሻሻ፥ ብልሹና ተንከራታች ሆኖ ተመለሰ። ዳሩ ግን ከሁሉም በላይ የሚያስደንቀው አባቱ ሊገናኘው ሮጠ፤ አቅፎም ሳመው። አባቱ (1) ከሁሉ በተሻለ ልብስ ከማጎናጸፉ (እድፉን ከመሸፈኑ)፥ (2) በጣቱ ቀለበትና (እንደገና እንደ ልጅ ተቀባይነት ማግኘቱን ያሳያል)፥ (3) ለእግሩ ጫማ ከማድረጉ (ነፃ ሰዎች ብቻ ጫማ ማድረግ ይፈቀድላቸው ነበር) በፊት፥ ልጁ ንስሐውን ለመናዘዝ አልቻለም። ከዚያም (4) «ይህ ልጄ ሞቶ ነበረና፥ ሕያውም ሆኖአል፤ ጠፍቶም ነበር ተገኝቶአልም» በማለት የሰባው ፍሪዳ ግብዣ እንዲደረግ አዘዘ።

«ሐላል ወይም ሐራም» - በእግዚአብሔር ፊት ትክክል ወይም ስሕተት

የ «ሐላል» (ሕጋዊ፥ ንጹሕ) እና «ሐራም፡» (ሕገወጥ፥ እርኩስ) ትርጉም መጽሐፍ ቅድሳዊ የኃጢአት ትርጉምና የሰውን ሙሉ ለሙሉ ኃጢአተኛ መሆን ለመግለጽ ሊጠቀም ይችላል። ኃጢአት ምን እንደሆነ ባላቸው ግንዛቤ ትልቅ ልዩነት ምክንያት እነዚህ ፅንሰ-ሐሳቦች በሙስሊሞች ዘንድ በቀላሉ የሚታወቁ አይደሉም። አንድ ሙስሊም ኃጢአትን የሚመለከተው ከትክክለኛው መንገድ እንደማሳበር አድርጎ ነው። አንድ ሰው የሚያደርገው ነገር ቢኖር ከዚህ ማሳበር ወደ ትክክለኛው መንገድ መመለስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ግን በተለየ ሁኔታ ያስተምራል። የሚያስተምረውም እኛ ሁላችን ኃጢአተኞች እንደሆንንና ከኃጢአታችን ነፃ መውጣት እንደሚያስፈልገን ነው (ሮሜ 3:23-24)። ይህ ፅንሰ-ሐሳብ ለሙስሊም

የሚከተለውን መግለጫ በመጠቀም ሊብራራ ይችላል:- ሙስሊም ጓደኛህ ወደ ገበያ አዳራሽ በመሄድ አራት ዓይነት የቆርቆሮ ሥጋ ቢያገኝ ምን እንደሚያደርግ ጠይቀው። የመጀመሪያው ቆርቆሮ ግማሽ የከብት ሥጋና ግማሽ የዓሳማ ሥጋ አለው። ሁለተኛው ደግሞ ሦስት እጅ የከብት ሥጋና አንድ እጅ የዓሳማ ሥጋ አለው። የመጨረሻው ደግሞ መሸፈኛው ብቻ የዓሳማ ሥጋ ቢሆን። ትንሽ የዓሣማ ሥጋ ያለበትን የመጨረሻውን ለመግዛት አይመርጥም ይሆን? ታማኝ የሆነ ሙስሊም አራቱም «ሐሊም» እንደሆኑ ወዲያውኑ ይመልሳል። ምን ያህል የዓሳማ ሥጋ እንደሚይዝ ወይም በዓሣማ ቆዳ ላይ ብቻ ተደርጎ እንደሆነ ምንም ለውጥ አያመጣም። ሁሉም የዓሣማ ሥጋ ስላለባቸው ሁላቸውም «ሐራም» ናቸው። በኃጢአትም በኩል እንዲሁ ነው። እግዚአብሔር ኃጢአት ሁሉ «ሐራም» ነው ይላል። ይህም እኛን በእግዚአብሔር ፊት ያልነጻን ያደርገናል።

እኔ 80 እጅ፥ ወይም 50 እጅ፥ ወይም 20 እጅ፥ ወይም 10 እጅ ኃጢአተኛ ብሆን የሚያመጣው ለውጥ አለን? በሰው ዓይን ሲታይ አዎን ለውጥ አለው። 30 እጅ ወይም 10 እጅ ኃጢአት ብቻ ያለበት ሰው የተከበረ ዜጋ ሆኖ ይቆጠራል። ነገር ግን በእግዚአብሔር ዓይን ሁሉም ኃጢአት «ሐራም» ስለሆነ፥ በሕይወታችን ውስጥ ያለው የኃጢአት መጠን፥ ወይም በሰዎች ዓይን ስንታይ ምን ያህል ቅዱስ መሆናችን ለእርሱ ምንም ለውጥ አያመጣም። በእግዚአብሔር ፊት ሁላችንም ኃጢአተኞችና ያልነጻን ነን። እግዚአብሔር ያልነጻን ነገር ወደ መንግሥቱ /ገነት/ ያስገባ ይሆን? (ራእይ 21፡27)።

* የዕንቁ - አውጪው - ልንከፍልለት የማንችለው ከእግዚአብሔር የተቀበልነው ቁጥር የሌለው ስጦታ

በሕንድ ምሥራቃዊ ዳርቻ የኖረው አንድ ዕንቁ አውጪ ሽማግሌ ለሚቀጥለው ሕይወት ለመዘጋጀት በማሰብ፥ ቀሪ ሕይወቱን ለሃይማኖት ሰጥቶ ለመኖር ወሰነ። በ «ቅዱስ» ጋንጀስ ወንዝ ዳርቻ ወደምትገኘው በነሬስ ወደተባለች «ቅድስት» ከተማ በጉልበቱ ተጉዞ እንዲሄድ በልቡ ወሰነ። እርሱም አንድ ክርስቲያን ወዳጅ ስለነበረው የመሰናበቻ ግብዣ አደረገለት። ይህ ሰው የዕንቁ አውጪው ብቸኛ የቅርብ ጓደኛ ነበር። ሌላ ዘመድ ያለው አይመስልም። ከምግቡም በኋላ ዕንቁ - አውጪው ዕቅዱን አጫወተው። ክርስቲያኑ ዕቅዱን ሊያስተወው ቢጣጣርም አልተሳካለትም። «ጉልበቶችህ ይቆስሉና በቁስል ሕመም ትሞታለህ» በማለት አስጠነቀቀው። ምላሹ ግን «ወደ ቅዱስ ጋንጀስ ስጓዝ በመንገድ ላይ ብሞት፥ ነፍሴ ትጸድቃለች» የሚል ነበር።

በኋላም በዚያው ምሽት ጓደኛው ከመሰናበቱ በፊት የዕንቁ አውጭው መደርደሪያውን በማንቀሳቀስ፣ ምንጣፉን ከወለሉ ላይ ጠቅልሎ አነስተኛውን የመሸሸጊያ ሥፍራ ገለጠ።

ትንሽ የታሸጉት ዕቃ አመጣና ከፈታት። በዚያም ውስጥ ትልቅ መጠንና ልዩ ውበት የተጎናጸፈ ዕንቁ ነበር «አንተ ብቻ ወዳጄ ስለሆንክ ይህን እንድትወስድ እፈልጋለሁ» አለው። «ይህ የከበረ ነገር ነው!» አለ ጓደኛው። አክሎም «እኔ እንዲህ ያለ ስጦታ መቀበል አልችልም» አለ። ዕንቁ - አውጭው በሐሳብ ተዋጠና ለመናገር ጀመረ! ወንድ ልጅ ነበረኝ። በባሕሩ ዳርቻዎች ተወዳዳሪ የሌለው የእንቁ - አውጪ ነበር። ከሁላችንም የበለጠ ጠልቆ መግባትና ለረጅም ጊዜ ውኃ ውስጥ መቆየት ይችል ነበር። አንድ ቀን እንደተለመደው አብረን በውኃ ውስጥ በመጥለቅ ላይ ነበርን። እኔ በታንኳው ውስጥ ሳለሁ፣ በኋላ የከፈትኋቸውን ዛጎሎች ለማምጣት ጠለቀ። ከዚያም እንዲህ ሆነ፡- በጣም ትልቅ ዛጎል በጥልቁ ውስጥ ተመለከተ። እርሱን ለማምጣትም ብሎ ቢሄድ፣ ከኮራሉ ጋር (የባሕር ውስጥ ቅሪተ አካል) ተያይዞ አልላቀቅ አለው። ሊያላቅቀው ሞከረ። ጊዜው እየመሸ ቢሄድም ተስፋ ሳይቆርጥ ሞከረ። በመጨረሻም ከረጅም ትግል በኋላ ይዞት መጣ። ሲተነፍስ ግን ከአፉ ውስጥ ደም ፈለቀ። ወደ ታንኳይቱ ስቤ ባስገባው በክንዶቼ ላይ ተዝለፍልፎ ሞተብኝ። በኋላም ያመጣውን ዘጎል ስከፍተው ይህን ዕንቁ አገኘሁ። ልሸጠው አልቻልኩም»።

ከተወሰነ ዝምታ በኋላም ጓደኛው፡- «ይህ ዕንቁ በሺህ የሚቆጠር ገንዘብ ለራሴ ስለፈለግሁት ሊሸጥ ይችላል። ዕንቁውን ስለምፈልገውም ብገዛህ ደስ ይለኛል። ትክክለኛ ዋጋውን ለመክፈል ባልችልም፣ አንድ መቶ ፓውንድ እንኳ ልስጥህ» አለው።

የእንቁ - አውጪው ዓይኖች በቁጣ ፍም መሰሉ። «ልጄ ለሞተበት ነገር ውዳቂ መቶ ፓውንድ ልትከፍለኝ ትፈልጋለህን? ለእኔ የሚያወጣልኝን ዋጋ ማንም ሰው ሊከፍለኝ አይችልም ነገር ግን ላንተ ልሰጥህ እፈልጋልሁ ..»

«አየህ» አለው ክርስቲያን ጓደኛው፣ «ልጁ ለሞተበት ለኃጢአትህ ጉዳይ ለእግዚአብሔር ዋጋ ለመክፈል ትሞክራለህ። ከክፍያ በላይ ለሆነው ነገር ለመክፈል በመሞከርህ እግዚአብሔርን የምታሳዝን አይመስልህምን?» እንቁ - አውጪውም ነገሩ ገባው። በጉልበቱም ወደ በነሬስ ከመሄድ ታቀበ። ይልቁንም ለኃጢአቱ ይቅርታ የሆነውን የእግዚአብሔርን ስጦታ ተቀበለ።

## ታማኝነት ለእውነት ምትክ አይሆንም

የዘላለም ራእይን በተመለከተ፣ አጠያያቂው ውብ ወይም በታማኝነት ተቀባይነትን ያገኘ ከመሆኑ ላይ ሳይሆን፣ እውነት ከመሆኑ ላይ ነው። ወደ አንድ ሥፍራ ለመሄድ ስንፈልግ፣ መጠየቅ ያለብን መንገዱ በግሩም ጌጣጌጦች የተከበበ መሆኑን ሳይሆን፣ ወደ ምንፈልግበት ሥፍራ የሚያደርሰን መንገድ እንደሆነ ነው። እውነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ትገኛለች። ምክንያቱም በተፈጸመ ትንቢት አማካይነት ራእይ የምናገኘው ከዚህ መጽሐፍ ውስጥ ብቻ ስለሆነ ነው።